# ትግላችን

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
ወርሃዊ መፅሄት
በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

---

## ዲሞክራሲና የአድርባዮች
## መንሸራተት

---

የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ፡
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN

ቁጥር 2 ኀኀቦተ 1970



# ጓድ ከበደ መንገሻ

“. . . ስጓዱ ከበደ በመጀመሪያና በተቀዳሚ ሊነገር
የሚቻለው ከጠራ አብዮታዊ ምሁርነቱ በላይ ለኢትዮጵያ
ሕዝቦች ነፃነት የታገለና ትግሉንም በቁርጠኛ አሳይቶ
ህይወቱንም በመስዋእትነት የከፈለ ፍጹም አብዮታዊ መሆ
ኑ ነው . . . ”

ከኢ.ኢ.ተ.ባ.

በኢ.ኢ.ተ.ማ. የመጽሔት ቦርድ አቸገ መጽሔት ለጓዴ ከበደ ወንገሻ መታሰቢያ ትሆን ዘንድ ያበረክታል



## ዲሞክራሲና የአድር ባዮች መንሸራተት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር 17ኛ ጠቅላላ ዓመታዊ ጉባዔ ፍጹም አብዮታዊ የሆነ ውሳኔ አንጓስተላለፈ ይታወቃል፡፡ ይህንን ውሳኔ ለይቶ ተኛ የሚያደርገው መሠረታዊ የሆኑ የአብዮቱ ጥያቄዎች ላይ በሙሉ ጥርት ያለ አቋም መውሰዱና አብዮታችን ፊትለፊት የተደቀነውን ዛሬ አስመሳይ ተራማጆች፣ዮዴሬ ቀኝ አድርባዮች፣የደርግ ቹችና አድሃሪው ቢሮክራሲ በማፋፋም ላይ ያሉትን የቅሰበባ አቋም በሳይንሳዊ ትንተና ላይ በመመርኮዝ በወቅቱ በአንግጭው አንጓለ ማመለከቱ ነው፡፡

ይህንን በገል አንባቢያን በተለይ እንዲገነዘቡት የምንሻው የዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄ ላይ ጠቆኞች በትግሉ የወደቁትንና በስፋቸውን ከሰፊው ሕዝብ ጉን አድርገው እየታገሉት ያለውን የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ እሁኑኑ መለቀቅ ጥያቄን የኢትዮጵያ አብዮት ትክክለኛ ሂደት ያስደነገጣቸውና የፖለቲካ ሥልጣንን የጨበጡት የቀኝ አድርባዮች፣የደርግ ቹቾችና አድሃሪው ቢሮክራሲ በበበበ አስበቡ እየተጠቀሙ ጥያቄውን ለማደብበበስ የሚያደርጉትን ሸርጉድ ነው፡፡

የዲሞክራሲ መብቶችን መለቀቅ አጣዳፊነት ሲያስረዳ ውሳኔያችን በወቅቱ አምስት መሠረታዊ ተጨባጭ ነጥቦችን መዘርዘሩ ይታወቃል፡፡ እነሱንም ለማስታወስ ያህል፣

ሀ/ የወዝ አደሩን መደብ ፓርቲና ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባሩን ለመፍጠር እጅግ አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር፡፡ለነሱም መፈጠር መሠረት የሆነውን ጠቋኝ የተራማጆች ሕብረትን ለማጠናከር ብሎም ከበርቅገቦችና አድሃሪያች ከፋፋይ ውክራ ያች ሊያዙኑ የሚችሉ ብቸኛ የትግል መሣሪያዎች እንደሆኑ፡፡ በይበልጥ ከሰፊው ሕዝብ ጋር ለመተሣሠር በዲሞክራሲያዊ የሁለት መስመር ትግል በዋነኛ የአብዮቱ ጥያቄዎች ላይ መወያየትና ብሎም ሰፊውን ሕዝብ በይበልጥ ለማንቃት ለማደራጀትና ለማስታጠቅ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ባስቸኳይ መለቀቅ እንዳለባቸው፡፡

ለ/ ለአድሃሪው ቢሮክራሲ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አሻጥሮች መጋለጥና መከሸፍ ለአዲስ ሕዝባዊ ሂደቶች በይበልጥ መጠናከር ምቹ ሁኔታን ስለሚፈጥር፡፡

ሐ/ በውስጥና በውጭ አድሃሪያች የሚሸረቡትን ሴራ በሚገባ ለመቋቋት ስለሚያስችሉ፡፡ በአብዮታችንና በአገራችን ላይ የሚያንዣብበው አደጋ በደርግ ብቻ ያውም በአድሃሪው ቢሮክራሲ አማካይነት የሚደመሰስ አደጋ በሳ ሰሆነ፣ በሰፊው ሕዝብ ሙሉ ተካፋይ ብቻ የሚወገድ አደጋ በመሆኑ የዲሞክራሲያዊ

መብቶች ለጭቁኖች ባስቸኳይ መለቀቅ ሰፊውን ሕዝብ ከዳር እስከዳር ለማንቀሳቀስ በርሱም ተሳትፎ ፀረ አብዮትን ከየአቅጣጫው ለመደምሰስ ዋነኛ መሣሪያ በመሆናቸው::

መ/ ሰፊው ሕዝብ በትግሉ ስለሚያጋጥሙት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በነፃ እንዲወያይ መፍትሄያቸውንም ከአብዮቱ መገፋት ጋር አያይዞ እንዲመለከት ለማድረግ ስለሚያስችሉ::

ሠ/ ሰፊው ሕዝብ አሮጌውን ስርዓት ደምስሶ አዲስ ሕይወት ለመገንባት በሚያደርገው ጥረት ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ኑሮን ለማጎልመድ ስለሚያስችሉ::

እነዚህንም ነጥቦች በሚገባ ከዘረዘረ በኋላ ዋናው የሚከተለውን ያሰፍራል::

" ... እነዚህና ሌሎች ምክንያቶች የዲሞክራሲያዊ መብቶችን መለቀቅ እጅግ አጣዳፊ በማድረጋቸው ሰፊው ሕዝብ ከዳር እስከዳር "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ በአስቸኳይ" በሚል መፈክር ስር ተሰልፎ በመታገል ላይ ነው:: ይህ እንደዚህ ሆኖ "ዲሞክራሲያዊ መብቶች አሁን ቢለቀቁ የአድሃሪያች መጠቀሚያ ይሆናሉ" የሚሉና ተመሳሳይ ስንኩል ሰበቦች <u>በሁለት አቅጣጫዎች</u> መሰንዘር ጀምረዋል:: እነዚህም ባንዱ በኩል በተሳሳቱ መነሻዎች ላይ የተመረኮዙ የጠላትን የፖለቲካ ሃይል ከማጋነንና በሰፊው ሕዝብ አብዮታዊነትና ታጋይነት ላይ እምነት ከማጣት የተነሳ በስሜታዊነት እንደገናም <u>በአድርባይነት</u> /ሥርዝ የተጨመረ ተገላችን::/ የተጋረጡ ተራማጆች ሲሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ በአድሃሪው ቢሮክራሲ ውስጥ የተሰገሰጉ የዲሞክራሲያዊ መብቶች መለቀቅ ስልጣናቸውን መከታ በማድረግ የምንሽርበውን ሰራ ያጋልጥብናል ብለው የሰጉ የነቁ አድሃሪያች ናቸው::"

ይህ ማህበራችን በወቅቱ ያስገነዘበው ጠቅ ዛሬ እውነትነቱን ተከትሉ የደረሰበት ደረጃ ሁላችንም የምናውቀው ነው:: የዚህን አባባል ትክክለኛነት ለመረዳት ዛሬ የኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ላይ በግልጽ መታየት የጀመረትን የቅልበሳ እርምጃዎች መመልከት ይበቃል:: ቅልበሳም ስንል በስንት ትግልና መስዋዕትነት የተገኘውን ሰፊው ሕዝብ ያቀፈውን <u>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ዓላማ</u> እንደሌለ አድርገው ወይም እንደተሠረዘ አድርገው አብዮቱ በረቂቅ መንገድ እንዲቀለበስ የሚጥሩትን እርምጃዎች ለመጠቆም ነው:: የዚህ አብዮታዊ ፕሮግራም ክፍል 3 "ጊዜያዊ ተግባሮች" ላይ የሰፈረውን ደግሞም ደጋግሞም መጥቀሱ እጅግ በጣም አስፈላጊ የሚሆነው የዲሞክራሲ መብቶችን አሁን መለቀቅ



የማደሸትን በሙሉ ዎን ያህል በአብዮቱ ትክክለኛ ፈር ለቀው እንደሚገኙ ለማሳየት ነው:: ምክንያቱም ይህን ፕሮግራም ፀረ ሰበት የሆኑ ሃይሎች በሙሉ የተቀበሉት፣ያፀደቁት፣የወደዱትና የሚታገሉለት አብዮታዊ ፕሮግራም ነውና:: ፕሮግራሙ እንዲህ ይላል፣

" ... ሕዝቡ በአብዮቱ መገፋት የሚችለው ንቁ ተደራጅቶና ታጥቆ ለትግሉ የተዘጋጀ ሲኖረው ብቻ በመሆኑና ይህ ዝግጅት የሰመረ ውጤት ሊሰጥ የሚችለው የሰፊው ሕዝብ ወገኖች በሙሉ ለመማር ለማስተማር፣ለመደራጀትና ለማደራጀት አስፈላጊ የሆኑት የዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለ አንዳች ገደብ ከሥራ ላይ ሲውሉ ብቻ ስለሆነ ለፀረ ፊውዳል ፀረ ቢሮክራሲያዊ ቡርዣ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ሃይሎች በሙሉ የመናገር የመጻፍ የመሰብሰብ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ የመደራጀትና የመሳሰሉት ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን በአስቸኳይ ከሥራ ላይ ማዋል::"

እንግዲህ ጠቅ ይህ ሆኖ ሳለ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ በተለይ ስለ ዲሞክራሲ ጥያቄ በመካሄድ ላይ ያለውን የሁለት መስመር ትግል /መቼም ምንም እንኳ ከአድርባዮ ወገን የሚሰነዘረው ተራ ውንብድናና ማጭበርበር መሆኑ ግልጽ ነው/ ቀረብ ብሎ የተመለከተ ማንም ጠቅ ግለሰብ ነገሩን የሚረዳው የአ/ብ/ዲ/አ ፕሮግራምን ዓላማ ከማይቀበሉና የዲሞክራሲያዊ መብቶችን መለቀቅ እንደጠር ከሚፈሩ አድርባዮች፣የደርግ ቀኞችና አድሃሪው ቢሮክራሲ በአንዱ ወገንና በሌላው ወገን ይህንን ፕሮግራም ከሚቀበሉትና በሥራ እንዲተረጎም ከሚፈልጉት ሃይሎች ማለትም ሰፊው ወዝ አደር ገበሬ ታጋይ ወጣቶች ሴቶች የቀበሌ መሪያች አብዮታዊ መለዮ ለባሾች ጭቁን ብሔረሰቦች መካከል እንደሚደረግ የሞት የሽረት ትግል ነው::

በሌላ አነጋገር አብዮቱን ለመቀልበስና ለማዳፈን ከሚፈልጉ ሰፊውን ሕዝብ እንደጠር ከሚፈሩ ፀረ ዲሞክራቲክ ሃይሎች በሙሉና አብዮቱ እንዲስፋፋና ኃይሉ ቶሎም ሰብሰብ እጥፍ ድርብ ወደፊት እንዲመጥቅ ከሚፈልጉ አብዮታዊ ሃይሎች መካከል የሚደረግ ትንቅንቅ ነው ማለት ነው::

ይህ የዲሞክራሲ ጥያቄ ከብዙ አንፃር በጣም ተራማጆች አስፈላጊነቱና አጣዳፊነቱ በየጊዜው በሳይንሳዊ ትንተና እየቀረበ መምጣቱ ያልተከሰተላቸው እሁንም ውር ውር ማለትን የያዙ ቀኝ አድርባዮችን ይበልጥ ለማወቅና ለማጋለጥ ይረዳ ዘንድ ለአንባቢያን ይህንን መጽሔት ለማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል::

ማንኛውም ሕዝብ ለነፃነቱና ለክብሩ ከውጭ ኃይሎች ጋር የሚያደርገው ትግል ረጅምና መራራ እንደሆነ በዙ መውደቅና መነሳት እንደሚያጋጥመው ተደጋግሞ የተነገረ ሃቅ ነው:: በአፍና በቲዎሪም ብቻ ሳይሆን ይህንን ጠቅ የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች ሊሳው ቀርቶ በየካቲት 66 ዓ.ም. ወዲህ ያሳለፋት የትግል ጊዜ በሚገባ አረጋግጦላቸዋል::

በተለይ በጓዶቻችን ደምና መስዋዕትነት ያሸበረቀ አኩሪ የትግል ምዕራፍ የተቀዳጀንበት ያለፈው የትግል ዓመት ህዝባዊ ድልና ጊዜያዊ መሸነፍ፤ማጥቃትና መከላከል፤ወደፊት መራመድና ባሉበት መርገጥ፤ መፈንደቅና አንገትን መደፋት...ተራ በተራ እየተፈራረቁ የታዩበት ዓመት ነበር:: አንድ ጭቁን ሕዝብ ወደወሳኙና ወደማያዳግመው የመጨረሻ ድል የሚጓዘው እየወደቀና እየተነሳ ነው የሚባለው ለዚህ ነው::

በትግሉ ጎዳና ላይ ይህ መውደቅና መነሳት በዙ መሰናክሎችና ገፅታዎች ይዞ ሊመጣ ይችላል:: የሰፊው ሕዝብ ሰፈር አጥቂ በሚሆንበት ወቅት ቅጥር ነፍሰገዳዮችን እያደነ በመደምሰስ በፀረ ሕዝቡ ሰፈር በሚነዛው ቀይ ሽብር ብቻ የሚወሰን አይደለም:: ይህንን ማድረግ የቻለው ሰፊ ሕዝብ፤ከዚህ ከፍተኛ የትግልና የድል ደረጃ የሚያደርሱትን የፖለቲካ፣ የድርጅት፤የርእዩተ ዓለም ሁኔታዎች አሟልቶ ተገኝቷል ማለት ነው:: የተቀዳጃቸው ድሎች ከአድርባዮችና አስመሳዮች አንስቶ እስከ ለየላቸው አድሃሪዎች ድረስ ያለውን የፀረ ሕዝብ መንጋ በነዚህ ሁሉ መስኮች በተገኙት ድሎች ፊት አንገታቸውን እንዲደፉ፤የሰፊውን ሕዝብ የበላይነት አምነው እንዲቀበሉ አስገድዷቸዋል ማለት ነው:: በዚህ አንፃር ደግሞ የሰፊው ሕዝብ ሰፈር በአድሃሪ ኃይሎች መጠቃት የሚተረጎመው የሲቀኛ አብዮታዊያንን ሕይወት በያለበት በየእለቱ በቅጥር ነፍሰገዳዮች በመነጠቁ ብቻ አይደለም:: ከዚህ ጋር ተያይዞ ያኔ በአጥቂነቱ ዘመን ሰፊው ሕዝብና ወገኖቹ የተቀዳጇቸው ድርጅታዊ፤ፖለቲካዊና ርዕዩተዓለማዊ ድሎች መፍረክረክና እንዳልነበረ ሆነው ማዘቀጥ ይጀምራሉ::

በእንደዚህ አይነቱ የአድሃሪዎች የአጥቂነት ወቅት ሰፊው ሕዝብ በደሙ የገነባቸው ድርጅቶች መፈራረስ ይጀምራሉ፤በትግል ከአድሃሪዎች የነጠቀው የፖለቲካ በላይነቱ በቀደመው ሥርዓት የስልጣን አውታሮች ፀረ ሕዝብ የበላይነት ይተካል፤ "አለቀላቸዋል" "ሰው ሁሉ አምኖ ተቀብሏቸዋል" የተባሉ የርዕዩተዓለም አቋሞች እንደገና ጥያቄ ውስጥ ገብተው አከራካሪ ይሆናሉ:: በመራራ ትግል



የተገኘው የርዕዩተ ዓለም ጥራት በአድሃሪዎች የአጥቂነት ዘመን እንደገና ለውዥንብር ቦታውን ለቆ ያለቃል::

ዛሬ በሃገራችን የምናየው ከዚህ የተለየ ጉዳይ አይደለም:: እየጠጠረ የመጣው የአድሃሪዎች አጥቂነት ዘመን ቅጥር ነፍሰገዳዮች ብቻ ይዞ አልመጣም:: ከሱ በምንም አይነት የማይነጠሉ የቀበሌ ማህበራት፤የአብዮት ጥበቃ ኮሚቴዎች፤የወዝ አደርና የአርሶ አደር ማህበራት መጠውለግ፤ የዲሞክራሲ መመንመን፤የአድሃሪው ቢሮ ክራሲ አሻጥር ዓይን ማውጣት፤አድርባዮችና የውስጥ አርበኞች በሚነዙት የርእዩተዓለም ውዥንብር ምክንያት የነበረው ጥራት መደፍረስና ትላንት እንዳይሸጡ እንዳይ ለወጡ ሆነው በአደባባይ የተዋረዱ "ቱዉሪዎች" እንደገና ማንሰራራት ... እነዚህ ሁሉ በርግጥ ዛሬ አብዮታችን በተከላካይነት ደረጃ እንደሆነ የሚያረጋግጥለን ምልክቶች ናቸው::

ዛሬ በዚህ መጽሔታችን የምናየው በየአቅጣጫው በማጥቃት ላይ ያሉት አድሃሪ ኃይሎች በአብዮቱ ሠፈር የነበረውን ጥራት ለማደፍረስ፤ሁሉ አምኖ የተቀበላቸው ይመስሉ የነበረትን ጥያቄዎች እንዴት እንደገና "አከራካሪ" ለማድረግ እንደሚሞክሩና በአብዮታውያን ሰፈር ሰርገው የገቡ የቀኝ አድርባይ አዝማሚያዎች በዚህ ግንባር አብዮቱን ለማጥቃት ተልእኮ እንደሚፈጽሙ ነው::

እንደሚታወቀውና በየትም አገር ታሪክ ተደጋግሞ እንደታየው አድሃሪዎች የሰፊውን ሕዝብ ሰፈር በርዕዩተዓለሙ መስክ ለማጥቃትና ውዥንብር ለመንዛት "ግራ" መሳይ በሆኑና በቀኝ አድርባይ ምሁራን "ግንባር ቀደምነት" ይሠራሉ:: እንደ ኢ.ህ.አ.ፓ. ያሉት ግራ መሳይ አድርባዮች በዚህ በኩል የፈጸሙትን በደል ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያውቀው በመሆኑና በተለይም ደግሞ ዛሬ በርዕዩተዓለሙ መስክ ኢ.ህ.አ.ፓ ጨርሶ የተተፋ በመሆኑ ጽሑፋችን ከሱ ላይ አያተኩርም:: ዛሬ ከግራ መሳይ ኢህአፓና ከጠቅላላው አድሃሪ ኃይሎች ጋር ከፍተኛ የርእዩተዓለም ትግል ተደርጎ በሰፊው ሕዝብ ልጆች ደም የተገኙትን ድሎች እንደገና ጥያቄ ውስጥ በማስገባት እንደገና ለአድሃሪ ኃይሎች የሚያመቺ ውዥንብር ለመንዛት የሚፍጨረጨሩ የቀኝ አድርባዮች ከጠቅላላው ከአብዮታችን መጠቃትና ከቀኝ ሃይሎች ማየል ጋር እያየሉ መጥተዋል:: ከአብዮቱ ሠፈር መጠቃት ጋር ስለሚመጣው የርዕዩተዓለም ውዥንብር፤የቀኝ አድርባይ ምሁራን በዚህ አድሃሪ ተልእኮ ስላላቸው "ግንባር ቀደም" ሚና ዛሬ እነዚህ የታሪክ አተላዎች "በዲሞክራሲያዊ መብቶች" ጥያቄ ላይ እና ነሳለን የሚሉት "ክርክር" በቂ ማስረጃ ይሆናል::ይህ ጽሑፋችን በዚህ መንሸራተት ላይ በማተኮር አብዮታችንን በርእዩተዓለሙ ግንባርም እንደገና ወደ አጥቂነት ለማሸ

ጋር የሚደረገውን የሃያኛ አብዮታውያን ጥረት ለማገዝ ይሞክራል ::

የዲሞክራሲ ጥያቄ የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት አንዱ መሠረታዊ ጥያቄ እንደሆነ ማንም የሚያውቀው ጉዳይ ነው:: ኢትዮጵያ ከፊል ፊውዳል ከፊል ካፒታሊስት አገር እንደመሆኗ መጠን፣ በምድሯ ላይ በመካሄድ ላይ ያለው አብዮት አዲሱ የዲሞክራሲያዊ አብዮት መሆኑን ጠቋሚ ተራማጆችና ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባካዩት ተሳትፎ የተቀበሉትና አየወደቁለት ያለ የታሪክ ጠቅ ነው:: የዚህም አብዮት ዓላማ ፀረ ፊውዳል፣ ፀረ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስትና ፀረ ኢምፔሪያሊስት መድረክ ላይ በማስተባበር፣ በጠቅላይ ወዝ አደር መደብ ፓርቲ ግንባር ቀደምነት፣ በወዝ አደር አርሶ አደር ሕብረት ላይ በተመረኮዘና የግራ ክንፍ ንዑስ ከበርቴውንና ሌሎችንም የተጨቆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ባጋርነት ባቀፈ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር መሪነት፣ በንቃ በተደራጀና በታጠቀ ሕዝባዊ አመጽ ፊውዳሊዝምን፣ ኢምፔሪያሊዝምንና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምን ደምስሶ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክን ማቋቋም ነው:: ይህም ዲሞክራሲያዊ አብዮት ከአሮጌው የከበርቴ አብዮት የሚለየው አንደኛው መሪው ከበርቴው መሆኑ ቀርቶ፣ ለአብዮቱ መሳካት ዋና መሠረት የወዝ አደሩ አመራር ብቻ መሆኑን የምንገነዘበት አንዱ ወቅት ማለትም የኢምፔሪያሊዝምና የሶሻሊስት አብዮቶች ወቅት በይፋ ካረጋገጠው ወዲህ ነው:: እርግጥ በኢትዮጵያም እንደታየው ሁሉ ይህንን አብዮት ወላዋዩ ንዑስ ከበርቴው በአመራር ደረጃ እስከተወሰነ ደረጃ /መጠነኛ ደረጃ ከአብዮቱ መሳካት ጋር ሲነፃፀር/ የሰፊው ሕዝብ ሃይል እስኪሰበ ረገገው ድረስ ይዞት ይመጣል:: ነገር ግን እስከዛሬ ቷ ታው ግቡ አያደርሰውም፣ ሊያደርሰውም አይችልም:: ምክንያቱም ሰፊው ጭቁን ሕዝብ ነቅቶ ተደራጅቶና ታጥቆ በወዝ አደሩ አመራር እንደ አንድ ሰው ሆኖ መምጣቱን እንደጠር የሚፈራው ወላዋይ ንዑስ ከበርቴ ከፀረ አብዮቱ ሰፈር ይዋል ይደር እንጂ መጓበሉ አይቀርምና:: በኢትዮጵያም የሚካሄደው የመደብ ትግል ለዚህ በቂ ማረጋገጫ ነው:: በልዩ ልዩ የሦስተኛው ዓለም አገሮች ታሪክ እንደተከሰተው ሁሉ አ/ዲ/አብዮት የአለም አቀፍ ሕዝቦች ትግል አንዱ አካል እንዱ አምሳል ለሶሻሊስት አብዮት ጥርጊያ ጎዳና የሚከፍት ግን ሶሻሊስት ያልሆነ አብዮት ነው:: ይህም አብዮት በመሠረቱ ፀረ ኢምፔሪያሊስት እንጂ ፀረ ካፒታሊስት አይደለም:: ማለትም በአለም አቀፍ ደረጃ የጥውለጋ ደረጃ ላይ የደረሰውን የካፒታሊዝም /ኢምፔሪያሊዝም/ ብዝበዛና ጭቆና ሲዋጋ አብዮቱ በሚካሄድበት አገር ውስጥ ካፒታሊዝም በጤናማ መንገድ በሰፊው ሕዝብ ቁጥጥር ሥር ሆኖ እንዲያድግ እንዲስፋፋ የአርባታ ሃይሎች ካለምንም ተፅእኖ እንዲጎጥቁ ይጥራሉ፤ ጠቋሚዎችም ለዚህ ጠቅ ይታገላሉ:: ይህንን የተቀደሰ ዓላማ ለመፈጸም



ና ለሶሻሊዝም ነባራዊ ሁኔታዎችን ለማሟላትና ትግሉን ወደፊት ለመቀጠል __እስከመ__ ጨረሻው ድረስ ካላንዳች መወላወል በግንባር ቀደምነት በቆራጥነት የሚታገለው ወዝ አደሩ ሲሆን በሶሻሊዝም __መሪነት__ ፀረ ሶስት ሃይሎች በሙሉ የጭቆናዎችን አንገብጋቢነት ለመሠረት እንደሚሰለፋና እንደተሰለፋ የነቻይና ኮሪያ... ወዘተ አብዮቶች በሚገባ ጥሩ አድርገው አረጋግጠውታል:: አዲሱ ዲሞክራሲያዊ አብዮት የሚያነሳቸው ጥያቄዎች ለሶሻሊዝም አብዮት ጥርጊያ መንገድ የሚከፍቱ መሆናቸው የተረጋገጠ ቢሆንም ጥያቄዎች ሶሻሊስት ናቸው ማለት አይደለም:: አንዱ ቡርዧ ዲሞክራቲክ አብዮት የሚያነሳቸው መሠረታዊ ጥያቄዎች ናቸው፣ ማለትም የዲሞክራሲ መብቶችና ነፃነቶችን የመሬት ጥያቄን... ወዘተ የመሳሰሉ:: እነዚህንም ጥያቄዎች ከበርቴው* የራሱ ጥያቄዎች ስለሆኑ ከመጀመሪያው አንስቶ እስከመጨረሻው ሊታገልላቸው በተገባው ነበር:: ነገር ግን በልዩ ልዩ አገሮች ታሪክ እንዳየነውና በኢትዮጵያችን ውስጥም እየተከሰተ የመጣው ጠቅ የከበርቴው ጥያቄ ሆነው የሚቀርቡትን ጥያቄዎች ሰፊው ጭቁን ሕዝብ ሲያነሳቸውና እስከመጨረሻውም ሊታገልላቸው ቁርጠ መነሳቱን ኪየሰቀጣዉ ሲያሰማ፣ የከበርቴው አንዱ ክፍል ደግሞ የገዛ ጥያቄዎቹን እየሸረ ከፀረ አብዮቱ ካምፕ መደባለቁን ሲመርጥና አብዮቱን ሲከዳ እናያለን:: ሰፊው ሕዝብ የከበርቴውን ጥያቄዎች ማንሳት ምን አስፈለገው ለሚሉ የአብዮቱ ሳይንሳዊ ሂደት ምንም ሳላገባቸው አድርባዮች ነገሩ ቀላል ነው:: ጋሪውን ከፈረሱ ለማስቀደም እንደማይቻለው ሁሉ ወደ ሶሻሊዝም ከመግባት በፊት መሟላት ያለባቸው የቡርዧ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ነባራዊ ሁኔታዎች ገና አሉ እንላቸዋለን:: ባገራችን የዲሞክራሲያዊ መብቶችም ሆኑ የመሬት ጥያቄ ለሶሻሊዝም መንገድ ጥርጊያ መንገድ የሚከፍቱ የትግል መሣሪያዎች ሆነው ይቀርባሉ ማለት ነው:: በኢምፔሪያሊዝምና በሶሻሊስት አብዮት ዘመን ውስጥ የሚካሄደውን አዲሱን ዲሞክራሲያዊ አብዮት የከበርቴው አንዱ ክፍል ሊያዳፍነው ሲፈልግና ሲክደው /ምክንያቱም በአንዱ መስኩ ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር ሙሉ ለሙሉ ስላልተቆራረጠና በሌላ መስኩ ከበስተጀርባው የነበረው የሕዝብ ሃይል እየመጠቀ ከፊትለፊቱ ሲደቀንበት ከለየላቸው ፀረ ሕዝብ ሃይሎች ጋር መደበለን ይመርጣልና/ ሌላኛው ክፍል ደግሞ ምንም እንኳን ለአብዮቱ ቢሰለፍም በፖለቲካም ሆነ በኢኮኖሚ ብዙ ድክመቶች ስለሚታዩበት ስለሚወላውልም ጭምር አብዮቱን በቆራጥነት እስከመጨረሻው ሊመራው አይችልም ለዚህም ነው የዚህን አብዮት አመራር እስከመጨረሻው ካላንዳች መወላወል የሚታገለው ወዝ አደር መደብ መውሰድ ያለበት የሚወሰደው። በኢትዮጵያችንም ውስጥ እየተከሰተ ያለው ጠቅ ይሄው ነው:: ነገሩን ጠበብ አድርገን ስንመለከተው ደርግ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ሃይሎች የሚያሳዩት ቀኝ ኋላ መዞርና ከአድሃሪው ቢሮክራሲ ጋር በመግጠም አብዮቱን መክዳት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ አብዮቱ

---

* ከበርቴው ሲባል በተለይ አዲሱ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ውስጥ ተራማጅ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉትን ንዑስ ከበርቴውንና ብሔራዊ ከበርቴውን ማለታችን ነው::

እንደፈነዳ ሰሞን የዲሞክራሲን ጥያቄ አንግበው የነበሩት ሃይሎች መካከል ዛሬ ይህንን ጥያቄ እስከመጨረሻው ሳይወላውሉ አሁንም የሚታገሉለት ወሳኞቹ ንዑስ ከበርቴዎች ሳይሆኑ በወዛደሩ ርእዮተዓለም የታነፁ ጭቁኖችና ሰፊው ጭቁን ሕዝብ ሆነው ስናገኛቸው እንደነቃም፤ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ለአብዮቱ መክዳት የቆሙ ኃይሎች እነሱ ናቸውና፡፡ ይህንን የእ/ሻ/አ ለማስታወሻ ከገለጽን ዘንድ ወደ ነጥባችን እንመለስ፡፡ ከዚህ በላይ እንደጠቀስነው ይህንን የእነሱ ዲሞክራሲያዊ አብዮት አጭር "ማስታወሻ" ከፍ ብለን የጠቀስነውን እንድንገመግመው <u>የዲሞክራሲ ጥያቄ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት አንዱ መሠረታዊ ጥያቄ እንደሆነ ማንም የሚያውቀው ጉዳይ ነው</u>፡፡ እንዲያውም ይህ ጥያቄ ከዋናው የዚህ አብዮት ጥያቄ <u>ከመሬት ጥያቄ</u> ጋር ባለው ግንኙነት የተነሳ እነ ሌኒን በዛውን ጊዜ ሲጽፉ "መሬትና የነፃነት" ጥያቄ እያሉ ይጽፉ እንደነበረ ይታወሳል፡፡ የዛሬን አያድርገውና በሃገራችንም የዚህ ጥያቄ ዋናነትና አንገብጋቢነት ለረጅም ጊዜ ታምኖበት የቆየ ጥያቄ ነው፡፡

የሰፊው ሕዝብ ሰፈር እየተጠቃ የወደቀበትን የርእዮተ ዓለም ውጅንብር ተመለከተው "በቂ ዲሞክራሲ ስለ አሁን ዲሞክራሲ አያስፈልገም" የሚሉ ደፋር የቀኝ አድርባዮች እስከመጡበት ወቅት ድረስ የዲሞክራሲን አስፈላጊነት ዓይን አውጥቶ የተቃወመ አድሃሪም ሆነ ተራማጅ እስከዛሬ አላየንም ነበር፡፡ ይህ ማለት ግን አድሃሪዎች የሰፊውን ህዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ደገፈዋል ወይም ደግሞ የሰፊውን ሕዝብ ነፃነት አልተቃወሙም ማለት አይደለም፡፡ ተቃውመዋል፡፡ ዛሬ ለዚህ ተቃውሟቸው ፈረስ ለውጠው በቀኝ አድርባይ ምሁራን ለመጠቀም እንደቻሉት ሁሉ ቀደምሲል የሰፊውን ህዝብ መብቶች ለመቃወም በገራ መሳይ አድርባዮች ይጠቀሙ እንደነበረ ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ አልረሳም፡፡ እንዲያውም ትላንት ከገራ መሳይ አድርባዩ ከኢ.ሀ.አፓ.ጋር የተደረገውን ክርክር፤ የተገኙትን ውሎች መለስ ብሎ ማየቱ ዛሬ በለየለት ቀኝነት የመጡትን ምሁራን ክህደትና መንሸራተት በሚገባ ሊያስጨብጠን ስለሚችል ዘር ብለን እንመለከት፡፡

አብዮታውያን ከገራ መሳይ አድርባዮችና ከቀኝ አድርባዮች ራሳቸውን ለይተው በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ላይ ይዘው የነበረውና አሁንም የያዙት አቋም /ደርግ ወደቀኝ መጠምዘዝ ስለፈለገ ሄካዊ አቋሙ ጠንክሯል!! / የአብዮታዊ ሃገ አቋም መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ በዚህ አቋም ውስጥ የዲሞክራሲ ጥያቄ እጅግ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ አብዮታውያን ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ተራማጅ



ዐርምጃዎችን በወሰደ ቁጥር የገራ አድርባዮችን ውካታና ጫጫታ ሳይፈሩ እስከ ሕይወታቸው ድረስ እየከፈሉ ከደርግ ጎን ቆመዋል፡፡ ነገር ግን ማንኛውም አብዮታዊ ዐርምጃና አዋጅ በማያወላውልና ዋስትና ባለው ሁኔታ በሥራ ላይ ለማዋል የሚችለው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ <u>ብቻ</u> ነው ብለው ስለሚያምኑ ሰፊውን ሕዝብ ለዚህ ታሪካዊ ሚናው ብቁ የሚያደርጉትን ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲጎናጸፉ ታግለዋል፡፡ በዚህም የቀኝ አድርባዮችን መሸቀጥቀጥ ሳያሳቁ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግን ፀረ ዲሞክራሲ አቋም በየአጋጣሚው አጋልጠዋል፡፡ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ ለሰፊው ሕዝብ የዲሞክራሲ መብቶች በግንባር ቀደምትነት ተሰልፈዋል፡፡

ዲሞክራሲ አስፈላጊ ስለመሆኑ ከእንቶለኪቸው ወኩንን ከራሱ አገስቶ ጠቀሳሳው ቀኝም ሆነ ገራው የተቀበለው ጉዳይ ስለነበረ ፀረ ህዝብ ሃይሎች የሰፊውን ሕዝብ መብቶች ለማፈንና የተቻለውን ያህል ለማዘግየት የተጠቀሙበት ዘዴ ዲሞክራሲ ለምን ዲሞክራሲ ለማን? ዲሞክራሲ መቼ? በሚሉት ጥያቄዎች ላይ ውጅንብር ለመንዛት በመሞከር ነበር፡፡

ነገር ግን <u>ከሰፊው ሕዝብ ትግል እያየለ መምጣትና መጠነኛ የሆነ ዲሞክራሲ በመገኘቱ የተነሳ</u> አድሃሪዎች በዚህ በኩል ሊነዙ የሞከሩት ውጅንብር እንዲጠራ የስስት ወር ይፋ ክርክር አልወሰደም፡፡ በ1968 ዓ.ም. በፋና በነበረው ዲሞክራሲያዊ ውይይት በመጨረሻም አብዮታውያን በነዚህ ጥያቄዎች ላይ በተለይ በገራ መሳዩ ኢ.ሀ.አፓ. አማካኝነት አድሃሪዎች የነዟቸውን ነጥቦች አጋልጠው ሃቀኛው የፖለቲካ መስመር አሸነፈ፡፡

ትዝ ይለን እንደሆነ እነ ሃሜቾ ማሆጋና እነ "ማርታ ዋለልኝ"ስ ነ ጃርዱ ሁንዲን" ዲሞክራሲ ለኢትዮጵያውያን በሙሉ ይሰጥና ይለይለን ሲሉ አብዮታውያን የዲሞክራሲን መደብ ጠባይ ገልጥለጥ አድርገው በሰፊው ሕዝብ ፊት በማሳየት ዲሞክራሲ ለበዝባዦች ሳይሆን መታወቅ ያለበት <u>ለሰፊው ሕዝብ ወገኖች ሁሉ ለሰፊው ሕዝብ ወገኖች ብቻ</u> መሆኑን አረጋገጡ፡፡ <u>ዲሞክራሲ ለጭቁኖች</u> የሚለው መፈክር የመሳው ጭቁኖች መፈክር ሆነ፡፡

ትዝ ይለን እንደሆን የዚያን ጊዜ ነጋዴዎ "ማርታ ዋለልኝ"ና መሳዩጁ ሰፊውን ሕዝብ ገራ ሊያጋቡት አብዮታውያንን ብቸኛ ሊያደርጉት የሞከሩት የቃላት ጨዋታ ነበር፡፡ በመጀመሪያ የ"ገራ" አድርባዮች <u>ዲሞክራሲ ያለገደብ</u>

በማለት የጠየቁት ዲሞክራሲን ለሁሉም መደቦች ነበር:: አብዮታውያን ደግሞ አድርባዮች ለዚሁ መፈክር የሰጡትን ትርጉም በመቃወም ዲሞክራሲ ለጭቁኖች አሉ:: በዚሁ የተረቱት የ"ግራ" አድርባዮች በክህደት አቋቁር ወዛገበር ነዛትን አንሄዱ በማለት "ዲሞክራሲ ያለገደብ የሚለውን መፈክር የማይቀበሉ ወገን ዲሞክራሲ ለጭቁኖችም ይገደብባቸው የሚል ወገን ነው እና ግን ዲሞክራሲ ያለገደብ በገለ ለሁሉም መደቦች ሳይሆን ለጭቁኖች ያለገደብ ይሰጥ ማለታችን ነው" በማለት በተዘዋዋሪ መንገዱ መረታታቸውን አምነው ከክርክሩ መድረክ ወረዱ::

አብዮታውያንም ዲሞክራሲ ያለገደብ ሲባል ለሁሉም መደቦች ይሰጥ ማለት ሳይሆን በጭቁኖች መብት ላይ ገደብ አይደረግ ማለት እንደሆነ በማስረዳት "ዲሞክራሲ ለጭቁኖች ያለገደብ" የሚለውን መፈክር አስተጋቡ:: ነገር ግን ይህ "ያለገደብ" የሚለው ቃል የተወረው እስከዚህም "ግራ" መሰሎቹ አድርባዮች የሚነዙትን ውዥንብር ለመቋቋም አልነበረም:: በዚሁ ክርክር ወቅት አድርባይ የተቀሙ ከደርግ አውሮፓች አገቡ እስከዛሬ የቀኝ አድርባይ ምሁራን ድረስ ተጣምረው ያገኙ ሌላ "ጠሪ" ነበር:: አብዮታውያን ዲሞክራሲ ለጭቁኖች ያለገደብ በሚሉ ለማስተጋባት የተገደዱት ይከንን ፀረ ሕዝብ ጠሪ ለመዋጋት ነበር::

አሁንም ትንሽ ወደታሪክ ዘወር በለን በገመለከት በታህሳስ ወር 1967 ዓ.ም. ደርግ "የኢትዮጵያ ሶሻሊዝም" በሎ የንዑስ ከበርቴ ሶሻሊዝም ባወጀ ጊዜ የዚሁ አቶጅ አንዱ ነጥብ "ብሄራዊ ሶሻሊስት ፓርቲ" የማቋቋም ጉዳይ የሚመለከት ነበር:: በዚሁ ጉዳይ ላይ ሃቀኛ አብዮታውያን በምንም ዓይነት የማያወላውል አቋም ነበራቸው:: ይኸውም በቢሮክራሲያዊ በሆነ መንገዱ ከላይ ለሰፊው ሕዝብ የሚወረወረውን ፓርቲ በመቃወም የመደራጀት መብት እንዲታወቅ መታገል ነበር:: ደርግና አንዳንዱ ቀኝ አድርባይ ምሁራን የዲሞክራሲን ጥያቄ የሚመለከቱት ከዚሁ "አንዱ ፓርቲ" ከሚለው አቋም ተነስተው ነበር:: በዚሁም የተነሳ ለሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ አስፈላጊ የሆነውን ዲሞክራሲያዊ መብት "ከመሰጠቱ" በፊት ይህ አንዱ ብሄራዊ ሶሻሊስት ፓርቲ መቋቋም አለበት የሚል ጠሪ ይነዛ እንደነበርና ሙሉ የመናገር የመሰብሰብ መብቶች በዚሁ ፓርቲ ቁጥጥር ስር ብቻ እንዲፈቀዱ ይሞክር እንደነበረ ትዝ ይለናል::/አሁንም "በወዝ አደር ፓርቲነት" መልኩን በማስቀየር በዶፋ የተያዘው ሰፊፋ ጫጫታና ውካታ ይኸው ባጭሩ በሰፊው ሕዝብ በስተጀርባ ይጠነሰስ የነበረው ሴራ የወለደው አደገኛ የቀኝ አድርባዮች ጠሪ ነው::/



እንዲሁም ዲሞክራሲ ለምን ? የሚለው ጥያቄ የተነሳው ይህንን "ጠሪ" አጋልጦ በኢትዮጵያ ያሉ ፀረ ፊውዳል፣ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ሃይሎች በሙሉ በየፈርጃቸውና በየደረጃቸው ተደራጅተው ዲሞክራሲያዊ በሆነ ዘዴ ህዝባዊ አብዮታዊ ግንባር እንዲመሠርቱም መሆኑን ለማበሰር እንደነበረ በዚያን ጊዜ ይወጡ የነበሩ ጽሑፎች ምስክሮች ናቸው::

በዚህም የተነሳ በተለይ የመደራጀትን ነፃነት በሚመለከተው ጉዳይ ከደርግና ከቀኝ አድርባይ ምሁራን በኩል በሰፊው ሕዝብ መብቶች ላይ ሊጫን የተቃጣውን ገደብ ለመቃወም አንዱ ቢሮክራሲያዊ ፓርቲ የሚለውን የንዑስ ከበርቴ አስተሳሰብ ለመቋቋም ለአብዮቱ እውነተኛ ዱላ ጠቀኛ የወዝ አደር ፓርቲ፣ ሌሎች ዲሞክራሲያዊ ፓርቲዎችና ህዝባዊ ድርጅቶች ነፃ በሆነ ዘዴ ተቋቁመው ህዝባዊ አብዮታዊ ግንባር የሚመሠርቱበትን የአብዮት ፋና ለመጥረግ "ዲሞክራሲ ለጭቁኖች" በሚለው መፈክር ላይ ሌላ ሃረግ መቀጠል አስፈለገ:: "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ" የሚለው አብዮታዊ መፈክር ከዚሁ የርእዮተ ዓለም ትግል በዱላ አድራጊነት ወጣ::

በዚህ መልክ የኢትዮጵያ አብዮታዊያን ለጭቁኖች ለዲሞክራሲያዊ መብቶች ያካሄዱት የርዕዮተ ዓለም ትግል ከዚሁ ላይ አልቆመም:: በተለይ አድሃሪ የደርግ አባላትና የቀኝ አድርባይ ምሁራን "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ" በሚለው ላይ ከተረቱ በኋላ "ዲሞክራሲ መቼ" በሚለው ጥያቄ ላይ ሌላ የመከራከሪያ ነጥብ ከፈቱ:: ከዚሁም ክርክር አንዳንዶች እስከ ዛሬ ድረስ እንቺ በለው የያዙት "ዲሞክራሲ ሲታወጅ አድሃሪያንም እንዳይጠቀሙበትና ህዝቡ በደንብ ሊጠቀምበት እንዲችል አስቀድሞ ትንሽ መንቃትና መደራጀት አድሃሪያቹን ትንሽ ማዳከም ያስፈልጋል" የሚል ጠሪ አመጡ:: ነገር ግን ይኸም ክርክር አላዋጣቸውም:: የኢትዮጵያን ጭቁን ሕዝቦች ትግል አፍነው ሊያዳክሙበትና ሊቀለብሱበት የሞከሩት ይህ ወጥመዱ ብዙ ሳይቆይ ተጋለጠ:: ህዝቡ አድሃሪያቹን ሊያደክም የሚችለው ይበልጥ ሲነቃና ሲደራጅ እንደሆነ ሊነቁ እስኪለቻሉ ድረስ ይበልጥ ለመንቃትና ለመደራጀት ደግሞ ዲሞክራሲያዊ መብቶች አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥሩ እሱ ማለት እስኪለቻሉ ድረስ አድሃሪያቹ እስኪዳከሙ ዲሞክራሲ አይቻልም የሚለው አዙሪት ብዙ የማያስኬዳቸው ሆነ:: ዲሞክራሲ መቼ ለሚለው ጥያቄ "ባስቸኳይ" የሚለውን የአብዮታውያንና የሰፊውን ህዝብ መልስ አይፋጠው ተቀበሉ::

እንግዲህ ዲሞክራሲ ለምን? ለማን? መቼ? የሚሉትን ጥያቄዎች በሙሉ የረዥም ጊዜ ትግል አድርገው፣ አድሃሪያችንን፣ የቀኝና የግራ አድርባዮችን ቲወሪያች ተራ በተራ አጋልጠው በነዚህ ጥያቄዎች ላይ አብዮታውያን የማያገሙ የሚመስሉ ዛሬ ግን እንደገና ጥያቄ ሲገቡ ቅምንያቸውን የርእዮተዓለም ድሎች ተቀናኙ::

ሌላውን ሁሉ ትተን የመላ ኢትዮጵያ ተራማጆች የጋራ ትግል የወለደውን የጋራ ትግል መድረክ የሆነውን ብዙ የሰፊው ህዝብ ልጆች እየተዋጉ የተሰዉለትን ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራምን ብንመለከት እነዚህ ሁሉ ድሎች ቁልጭ ባለ መልክ ሰፍረው እናገኛቸዋለን:: በነዚህና በሌሎች የርዕዮተዓለም ጥያቄዎች ላይ የግራ አድርባዮች ድል ተመትተው በጋለ ቱግ አጥቂነት እፍላ ውስጥ ሰፊው ሕዝብ እንዳለ በታወጀው በዚህ ፕሮግራም ውስጥ እነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች ያለአንዳች ማወላወል አብዮታዊ መልስ አግኝተው እናያቸዋለን:: ዛሬ የቀኝ አድርባዮች በዲሞክራሲ ጉዳይ ላይ የሚያነሱት ውዥንብር ወደዓም ጠለም ይኸንን ፕሮግራም እንደካዱና ሊያፈርሱት እንደሚፈልጉ ነው የሚያሳየን::

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ገና አሳማዎች በሉ ሲጀምር በጊዜው የነበረውን ጥራት አበጥሮ በሚያሳይ ሁኔታ ከአብዮታችን ዓላማዎች አንዱ "... የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነቱን እኩልነቱን አንድነቱን በሰላምና በለጸገና የሚያረጋግጥበት በየደረጃውም ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት የሰፊው ሕዝብ ወገኖች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለ አንዳች ገደብ ተከብረው በሥራ ላይ የሚውሉበት ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መቋቋም::" እንደሆነ ያረጋግጣል:: ሰፊው ሕዝብ አስቀድሞ ነቅቶ ተደራጅቶ እንጂ ከዚያ በፊት "ላላወቀና ላልነቃ" ሕዝብ እንዴት ዲሞክራሲ ይሰጣል ለተባለው የአድሃሪያችና የቀኝ አድርባዮች ክርክር በማያሻማ ሁኔታ መልስ ለመስጠት ፕሮግራሙ ጊዜያዊ አጣዳፊ ተግባሮች ብሎ ሲዘረዝር "... ሕዝቡ በአብዮቱ መገፋት የሚችለው ነቅቶ ተደራጅቶ ታጥቆ ለትግሉ የተሟላ ዝግጅት ሲኖረው ብቻ በመሆኑ ይህ ዝግጅት የሰመረ ውጤት ሊሰጥ የሚችለው የሰፊው ሕዝብ ወገኖች በሙሉ ለመማር ለማስተማር ለመደራጀትና ለማደራጀት አስፈላጊ የሆኑትን ዲሞክራሲያዊ መብቶች



ያለአንዳች ገደብ ከሥራ ላይ ሲውሉ ብቻ ስለሆነ ለፀረ ፊውዳል ፀረ ቢሮክራሲያዊ ቡርዧ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች በሙሉ የመናገር የመጻፍ የመሰብሰብ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ የመደራጀትና የመሳሰሉት ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን በአስቸኳይ ከሥራ ላይ ማዋል::" ምንም መፈናፈኛ የማይሰጥ አብዮታዊ አቋምን ይገልጻል:: አንዱ "የወዝ አደር ፓርቲ" እና ቋሚ ከዚያ በኋላ ዲሞክራሲ "እንፈቅዳለን" የሚለውን የንዑስ ከበርቴ ፈሊጥ አብዮታውያንና ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዉርስ እንደማይቀበሉ በማስረዳት ፕሮግራሙ በሃገሪቱ የሚገኙ ፀረ ፊውዳል ፀረ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስትና ፀረ ኢምፔሪያሊስት ወገኖች በፓርቲዎችና በሕዝባዊ ድርጅቶች ለመደራጀት ያላቸውን መብት አረጋግጦ እንዲያውም መንግሥት እነዚህን ሁሉ እንዲረዳ ያስ ይገባል:: ይህ ሁሉ ታውቆ ደግሞ በዚህ ጥያቄ ላይ ዛሬ ነገ እንዳይባል ለሰፊው ሕዝብ የነዚህ መብቶች መታወቅ ጉዳይ ከአብዮቱ "አጣዳፊ ተግባሮች" አንዱ መሆኑን ፕሮግራሙ በይፋ ያስታውቃል::

የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት/በወቅቱ የነበረው ማለታችን ነው/ ይህንን በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም የተገኘውን ድል ሳይውል ሳያድር ከሥራ ላይ እንዲውል "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለአንዳች ገደብ" የሚለው ዓላማ ከሥራ ላይ የሚውልበትን አዋጅ ከፕሮግራሙ እኩል አርቅቆ እንዳቀረበ ይታወቃል:: /ትግላችን ዘና ቁጥር 2 ጥቅምት 1970 ዓ.ም. "የዲሞክራሲ መብቶች ረቂቅ አዋጅና አጭር መግቢያ" ተመልከት/ ይህ አዋጅ እንዳይታወጅ ያደረጉት የህዝቡን ዲሞክራሲያዊ መብቶች አፍነው ለመያዝ ይሞክሩ የነበሩት እነ አለማየሁ ሃይሌ እንደነበሩ ከዚህ በፊት ተነግሯል:: መብቶች በአስቸኳይ ከሥራ ላይ መዋል እንዳለባቸው ጥር 27 ቀን 1969 ዓ.ም. ሌ/ኮ መንግሥቱ ቃል ገብቶ እንደነበር ይታወቃል:: ከዚያም የኢትዮጵያ ጭቁኖች አብዮታቸውን ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት አሸጋግረው በነበረበት በየካቲት ወር 1969 ዓ.ም. የወጣው የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ወርሃ ገበር በተለይ በጊዜው አብዮቱን ለመቀልበስ "አሰፍስፈዋል" /ዛሬ ምንሊባሉ ይሆን?/ የተባሉትን አድሃሪያች ለመደምሰስ አስፈላጊ የሆኑት ዲሞክራሲያዊ መብቶች "በአስቸኳይ" እንዲታወጁ ለመታገል ወስኖም እንደነበረ አንዘነጋም::

ባጭሩ የፀረ አብዮት ሃይሎች አጥቂነት እየጠጠረ መጥቶ በእንዲህ ዓይነት ወቅት ምን ጊዜም ቢሆን ለመንሸራተት "ግንባር ቀደም" የሆኑት የቀኝ አድርባይ ምሁራን እነሱም ያቀማቸውን በርእዮተ ዓለሙ አንጻር የሰፊውን ሕዝብ ሰፈር ማጥቃት እስከጀመረበት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በዲሞክራሲያዊ መብቶች ጥያቄ ላይ በጣም ከፍተኛ የሆነ የርእዮተዓለም ጥራት እንደነበረ ሁላችንም የምናስታውሰው ነው። ዛሬስ? ዛሬ ሌላ ነው። ከላይ እንዳልነው የአብዮት ሰፈር ሲጠቃ በሁሉም መስክ እንደሆነው ሁሉ ዛሬ በቀኝ አድርባይ ምሁራን ግንባር ቀደምትነት እነዚህ በስንት ታጋይ ጓዶች ደም ሊቀዳጁ የቻሉት የርዕዮተ ዓለም ድሎች እንደገና "አከራካሪ" እየሆኑ እናያቸዋለን።

ዛሬ በዚህ አጭር ጽሑፋችን በዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄ ላይ ያለውን መንሸራተት ለማሳየት እንጂ በዚህ ጉዳይ ላይ እንደገና ክርክር ለመግጠም አንፃ ይደለ / ምክንያቱም ብዙ ጠቆች ተመላልሰውበታልና ትግላችን ዜና ቁጥር 3 ሚያዝያ 1970 ዓ.ም. "የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ" ተመልከት / አንባቢያን እንዲረዱልን እንጠይቃለን። በዲሞክራሲ መብቶች ጉዳይ ያለቀላቸውን የክርክር ነጥቦች እንደገና ፈልፍሎ በማምጣትና በአብዮቱ ሠፈር ውዥንብር ለመንዛት የሚደረገውን ከንቱ ሙከራ ቁልጭ አድርጎ ለማየት አድርባዮች "አጥቂነታቸውን" የጀመሩበት ወቅት ውስጥ መለስ ብሎ መመልከት እጅግ በጣም ጠቃሚ መስሎ አግኝተነዋል። የሕዝብ ድርጅት ጉዳዮች ጽ/ቤትን አብዮታዊ ተግባሮች አንጸባረውት የነበሩት ጥቂት አብዮታዊያንን ደርግ በሃይል ካሰናበታቸው በኋላና እነሱም ይህን መድረክ ለመልቀቅ በተገደዱበት ወቅት ይህ ተቋም የአድሃሪያንና የቀኝ አድርባይ ምሁራን መፈንጫ ሆኖ እንደቀረ ዛሬ ማንም የሚያውቀው ነው። እነዚህም አድርባዮች ይህንን መድረክ የውዥንብር መንዣ ማድረግ እንደጀመሩ "አብዮታዊት ኢትዮጵያ" ቁጥር 33 ላይ የቀኝ አድርባይ ምሁራን የሚመጨረጨሩትን መለስ ብለን እንመልከት።

በዚች "አብዮታዊ ኢትዮጵያ" ቁ.33 ላይ አንዱ "አንባቢ" መስከረም ሁለት ቀን "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ" "ዲሞክራሲ መብቶች ለሰፊው ሕዝብ" "ሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን በትግሉ ይቀዳጃል" የሚሉ መፈክሮች አይቼ ግራ ገብቶኛልና ይብራራልኝ ይላል። የ"አብዮታዊት ኢትዮጵያ" አዘጋጆች / ማለት የቀኝ አድርባዮች/ ለዚህ የአንባቢ "ጥያቄ"



ሲመልሱ እንዲህ ይላሉ፣

"የዲሞክራሲ መብቶችን በሚመለከተው ጥያቄ ላይ ባሁኑ ጊዜ ገለጸ የሆኑ ሶስት አቋሞች አሉ። እነሱም "የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ" ፣ "የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች" ፣ "የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ በትግላችን" የሚሉት ናቸው" ካሉ በኋላ የአብዮታዊት ኢትዮጵያ አዘጋጆች የዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄ በተራማጆች መሃል ልዩነት እየፈጠረ መሄዱን ነገሩ ጥናትና ጥንቃቄን የሚጠይቅ መሆኑን ወደፊት ጥያቄው በጋዜጦች አማካይነት ስለሚቀርቡ አንባቢያን ያን ጊዜ ልዩነቶቹን ለማወቅና ለመረዳት ብሎም "ትክክለኛውን" አቋም ለመውሰድ ትችላላችሁ በማለት ይሰናበቱናል።

በዕውነቱ እንጂ ሃቹ እምና በነዚህ ጥያቄዎች ላይ የተካሄደውን ያለቀ የደቀቀ "ውይይት" "ጥናት" የተከታተለ ሰው ቀርቶ ከላይ ባጭሩ የተረከናለትን የትግልና የርዕዮተዓለም ድል ታሪክ የተረዳ ሰው ከፍ ብለን በጠቀስነው ጥቅስ ተመርኩዞ መጽሐፍ ሊጽፍ ይችላል። መዓት አርዕስቶች አሉት። ስለ ቀኝ አድርባዮች ጽሀይት፣ አብዮት ሲጠቃ ለማሳየት ስለሚመክሩት ከንቱ የንዑስ ከበርቴ ብልጣብልጥነት። አንዱ ታጋይ ህዝብ ዘወር ብሎ የመጣበትን የትግል ጉዳና ለመመልከት ስላለው የማስተዋል ችሎታ ያላቸው የንቀት አስተያየት። ምሁራን በአብዮት ሠፈር ይዘው የነበሩትን የትግል ቦታ በፍርፋሪ ከሸጡ በኋላ ያንን ለመሸፈን ስለሚያደርጉት መፍጨርጨር ምስኪንነት ...ወዘተ ብዙ ድርሰቶች ለመጻፍ ይቻላል። እኛ ግን ወደታየው አሳፋሪ መንሸራተት እንመለስ።

ጥቂት አብዮታዊያን በዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄ ላይ በሰፊው በጋዜጦች መድረክ አቋማቸውን ገለጸ አድርገው እንዳስቀመጡት ብሎም ለፍስፍሰ የቀኝ አድርባዮችን እንዳጋለጡና እንዳሸበሩ ይታወቃል። ከዚህም ጊዜ ወዲህ ቀኞች ተደናብረው የጋዜጣ መድረኮችን ለጠቆች መዝጋታቸው ይታወቃል። ስለሆነም አድርባዮች ራሳቸው "ከውይይትና" "በጥናት" እያሉ በመጠጠት መንገዱ እንኳን ይከመታቸውን ይፋ አድርገው አስታውቀዋል። ሃቀኛ አብዮታውያን በሃቀኛ የሰፊው ህዝብ ልጆች ደም የተጻፈውን የጠራ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም እንዲንም ቃል ባያዝገፉ

እስከመጨረሻው ይጓዛሉ፡፡ ዛሬ በዚህ ፕሮግራም ላይ ቁልጭ ብሎ የተነደፈውን ከሁለት ዓመት ያህል በፊት አጪኳፊ ተብሎ የነበረውን የዲሞክራሲን ጥያቄ እንደገና መልሶ ጥያቄ ውስጥ ማግባት ፕሮግራሙን ዉርስ ማካዱ ነው፡፡ የቀኝ አድርባዮች ''ፕሮግራሙ ልክ አይደለም'' ''የሚታረም ነገር አለው'' ''አሻሚ ነው'' ይበሉን ና ክህደታቸውን ይፋ ያውጡ እንጂ አብዮታውያን ከዚህ ከብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በምንም ዓይነት ነጥለው በማያዩት የዲሞክራሲ ጥያቄ ላይ ከአድር ባይ ምሁራን ጋር ወደ ኋላ በምንም አይነት አይረገጡም፡፡ በሰፊው ሕዝብ በፊት የርእዮተዓለም ውዥንብር ሲነዙ አብዮታውያን ዝም ብለው አይመለከቱም ከፕሮግራሙና በዲሞክራሲ ጉዳይ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከተቀበለው አቋም እየተነሱ የቀኝ አድርባዮችን ክህደት ከማጋለጥ በፍጹም አይመለሱም የዚህ ጽሑፍ አንዱ ዓላማ ይኸው ነው፡፡

የቀኝ አድርባይ ምሁራን ዛሬ በዲሞክራሲ ጥያቄ ላይ ''ሶስት የተለያዩ አቋሞች አሉ'' ይላሉ፡፡ እንደእውነቱ ከሆነ ግን ያሉት ሁለት አቋሞች ብቻ ናቸው፡፡ አንዱ በብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ ቁልጭ ብሎ ቁርጥ የሰፊው ሕዝብ ልጆች የተሰውለት አብዮታዊ አቋም ነው፡፡ ሌላው ይህን ፕሮግራም፣ ሰፊውን ህዝብና የኢትዮጵያን አብዮት ዉርስ የከዳና ወደ ጭቁን ሕዝቦች ጠላቶች የተንሸራተተ የአድርባይ ምሁር አቋም ነው፡፡

በመሠረቱ እነዚህ ሶስት የተለያዩ አቋሞች የተባሉት ነገሮች የሚያወሩት ስለ አንዱ ነገር ሳይሆን ለሶስት የተለያዩ ጥያቄዎች መልሶች ናቸው፡፡ የመጀመሪያው / ማለትም ''የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለ ገደብ አሁኑኑ የሚለው/ ዲሞክራሲ መቼ? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ነው፡፡ ሁለተኛው / ማለትም ''የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች''/ ዲሞክራሲ ለምን? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ነው፡፡ ሶስተኛው ደግሞ / ''የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ በትግላችን''/ ዲሞክራሲ እንዴት ? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ነው፡፡ለነዚህ ሦስቱ ጥያቄዎች የኢትዮጵያ አብዮታውያን የዛሬ ሁለት አመት ገደማ በፕሮግራሙ ላይ ''አጪኳፊ'' የተባሉት የዛሬ ዓመት ገደማ በማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች መርሃ ግብር ላይ ''አስቸኳይ'' የተባሉት ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ በለው እየታገሉና እየተሰው አብዮታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡



እርግጥ ዛሬ የቀረበው የጊዜው አንገብጋቢ ጥያቄ ዲሞክራሲያዊ መብቶች አሁን ይታወጁ ወይስ አይታወጁ በሚለው ላይም ነው፡፡ በዚህ የጊዜው ዋና ጥያቄ አንፃር የቀኝ አድር ባዮች ስለ የሚሉት ልዩነት የሚያስቅ ነው፡፡ ዲሞክራሲ መቼ? ተብሎ ሲጠየቅ ዲሞክራሲ ለምን? ዲሞክራሲ እንዴት? ለሚለው ጥያቄ ይመልሳሉ፡፡ ከአንበሳና ከነብር ማን ያሸንፋል ቢለው ዝሆንን ማገቻሉት! እንዳለው መሆኑ ነው፡፡ ያልተጠየቀትን ነው የሚቀባጥሩት!

በተለይ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ በትግላችን የሚለው ''አቋም'' ትላንት ሸንጡን ገትሮ ይታገልለት የነበረውን መፈክር ከዱቶ ከትግል መዱረክ የወረደው አድርባይ ክህደትን ለመሸፋፈን የምን ተፍረተን የወረወረው መፈክር ነው፡፡ በዚህ አንፃር የተሰለፉት የማሌሪድ አድርባዮች እስከ ሚያዝያ ወር 1969 ዓ.ም. በሰባናቸው ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ! እያሉ ያስተጋቡ እንደነበር ይታወሳል፡፡ ከመላ ኢትዮጵያ ሶሺሊስት ንቅናቄ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ያቋረጡትም መኢሶን በዚሁ መፈክር በመቀጠሉና እነሱ ይከንን መፈክር በመከዳታቸውና በመንሸራተታቸው እንደሆነ የታወቀ ነው፡፡ እንደ ዚሁም በመሆኑ ሰፊው ህዝብ ለነዚህ መብቶች በያለበት እየተዋደቀ አብዮታውያን ልጆቹ ከሱ ጋር ተዋህደው ትግላቸውን ሲያፋፍሙ አብዮታዊ ነኝ የሚል ሁሉ ዛሬ ለነዚህ መብቶች እንዲታገል ተደጋጋሚ ጥሪ ሲያደርግለት እናያለን፡፡በእንደዚህ ዓይነት ወቅት ለሰፊው ህዝብ መብት እንታገል ቢባሉ ''የለም እና የተለየ አቋም አለን በትግል ነው የምናምነው ከናንተ ጋር አንታገልም'' ማለት የአድርባዮችን ክህደትና ከትግል መዱረክ መሰናበት ሊሸፍን የሚችል ''ከርከር'' አይደለም፡፡ በዚህ ለማወናበድ አስበው እንደሆነ ወይ እነሱ ተስፋ የሌላቸው ቁኖች ናቸው ወይ ደግሞ ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ ንቀት አላቸው ማለት ነው፡፡

የሆነ ሆኖ ዲሞክራሲያዊ መብቶች በትግላችን ሲሉና በዚህ'' አብዮታዊ'' መፈክር ስር ሰው ለመቀስቀስ ''ሲታገሉ'' እስከዛሬ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይሰዋ ሳይሞት ሳይታገል በታጋይ ልጆቹ ደም ሳይከፍል ከጠላቶቹ በሰላም ያገኘው ምን ነገር አለና ነው ዛሬ ለዚህ መብት እንደ አዲስ ነገር ታገል የሚባለው ? ደግሞስ ልብ ብሎ ላየው ሰው ትግቱ አስፈቻው መፈክርና ወደትግል

ጋባዡ መፈክር የትኛው ነው? "ዲሞክራሲ አሁኑኑ" ሲባል ሌላ ምንም ትርጉም የለውም:: አሁኑኑ ትግላችንን እናፋፍም ማለት ነው:: ይህንን መፈክር ሲያስተጋባ ቆይቶ "አሁኑኑ" የሚለውን ትግል የሚያፋፍም ጥሪ ትቶ "ዲሞክራሲ በትግላችን" ማለት ግን የታወቀውንና ያለቀለትን ነገር መድገም ብቻ ሳይሆን ጥራት ካለው የትግል ጥሪ ሰፊውን ሕዝብ ለማወናበድና ትግሉን ለማዘረክረክ የተቃጣ ትጥቅ አስፈቺ ፈሊጥ ነው:: እነዚህ አድርባዮች ይህ ተዐምር ከተገለጸላቸው ዘንዳ ከአብዮታውያንና ከሰፊው ሕዝብ ጋር ተዋህደው ለምን አሁን አይታገሉም? አብዮታውያንስ አሁን በለው ትግላቸውን ሲያፋፋሙ የሰጡ ዉዋታ የያዙ መስሏቸው ይሆን?

በዚህ መፈክር ስር የተሰለፉት ጥቂት አድርባዮች ተገሽራቱ ከዘቀጡበት የታሪክ አተላነት የምንተፍረታቸውን በመረወረት በዚህ አስቂኝ መፈክር ራሳቸውን ይበልጥ ከማጋለጥ በስተቀር ማንንም ያወናበዱ ስላልሆነ እና አብዮታውያን "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች አሁኑኑ" በሚለው መፈክር ስር በመታገል ላይ እንደሆንን በዚህ የትግል ሜዳ ግን እነሱን "በትግላችን" ባዩትን በንፈለገ በንፈለገ እንዲጠናቸው አስታውሰናቸው እንለፍ:: በዚህ ጉዳይ ላይ ከነዚህ አድርባዮች ኩምክና ይልቅ አስጊና በሚያባየው የቷወሪ "ቀንበር" አደገኛ የሆነ ሌላ አድርባይ አዝማሚያ ስላለ አንባቢ ወደሱ እንዲያተኩር እንጠይቃለን::

ይኸ የቀኝ አድርባይ አዝማሚያ "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለ አንዳች ገደብ" ዝብሉ በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም የተገኘውን ዉል አፈር ለማለበስ በተለይ የወዝአደር ሊግ መሪዎች የጀመሩት አደገኛ የመገሽራቱት አዝማሚያ ነው:: በነዚህ አድርባይ መሪዎች "አስተካበብ" "ያለገደብ" የሚለው አነጋገር "አሻሚ" ስለሆ የዛሬ ሁለት ዓመት ገደማ የተደመደመው የክርክር ክፍል እንደገና መከፈት አለበት በፕሮግራሙ ላይ "ያለአንዳች ገደብ" የተባለውም እንግዲህ "አሻሚ" ሊሆን ነው ማለት ነው:: አድርባዮቹ ይህን ትተን "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች" እንበል ይላሉ:: ደፍረው አለወጡ ሬትም እንጂ "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ" የሚለውን የተቃወሙ ሰውና "ያለገደብ" የሚለውን አነጋገር "እንዲወጣለት" የሚጠይቁ አድርባይ



ዘር ዘር "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች በገደብ" ማለቱ እንደሆነ ግልጽ ነው:: "ያለገደብ" የሚለው" ቃል" ይውጣ ያለ ነው አማርኛው ለጀርሶችን ቀጭ ነው ቢል ተባለ በስተቀር

ለጭቁኖች ተገድቦ ይሰጥ ወይስ ያለአንዳች ገደብ ይሰጥ የሚለው ጥያቄ ለምን እንደተነሳ በተለይ ደግሞ "ያለአንዳች ገደብ" ያሉት ኃይሎች ጀክ እንዲገባ የተከራከሩት የሰፊውን ህዝብ ወገኖች ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለማኩላሸትና በንውስ ከበርቴውና በቢሮክራሲው ቁጥጥር ስር ለማምጣት ይደረግ የነበረውን የአንዳንዱ አድሃሪ የደርግ አባላትና የቀኝ አድርባይ ምሁራን ሙከራ ለመቋቋም እንደሆነ ከፍ ብለን አሳይተናል:: ዛሬም የኢትዮጵያ አብዮት የያዘውን አቅጣጫ ስንመለከት የምንረዳው ሃቅ ነው:: በዚያን ጊዜ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ተገድቦ ይሰጥ ይሉ የነበረት ፀረ ሕዝቦች ዋና ዓላማቸው የህዝቡን የመደራጀት መብት ለመገታትና ከሱ ቀደመው ተደራጅተው ከዚያ በኋላ በዚያ በቢሮክራሲያዊ ፓርቲያቸው አማካይነት "ለከ ያለው" ዲሞክራሲ "ለመፍቀድ" እንደነበረ አሳይተናል::

ዛሬም የወዝ አደር ሊግ መሪዎች ዲሞክራሲ ለጭቁኖች በገደብ ይሰጥ ብለው ለዚያውም ደግሞ አሁኑኑ መታወጁን ሲቃወሙ የዚህን ጥያቄ አንገብጋቢነት መካዳቸው ብቻ እንዳልሆነ ግልጽ ነው:: የወዝ አደር ሊግ አድርባይ መሪዎች በዚህ አቋማቸው የሚሞክሩት ከብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መታወጅ በፊት ይሞከር እንደነበረው የኢትዮጵያን ጭቁኖች በየፈርጃቸውና በየደረጃው ለመደራጀት ያላቸው መብት ለማፈን ነው::

አሁንም ከላይ ወዳነሳነው ነጥብ እንመለስ:: በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለ አንዳች ገደብ የተባለው ሰፊው ህዝብ እንዲነቃና እንዲደራጅ ለማገዝም እንደሆነ ቁልጭ ብሎ የሠፈረ ነው:: የወዝአደር ሊግ መሪዎች ነገሩን እንዲህ አድርገው አያዩትም:: ወዝ በተባለው ልሳናቸው በይፋ እንዳስቀመጡት ዲሞክራሲ "ከመስጠቱ" በፊት የወዝ አደሩ ፓርቲ መቋቋም አለበት:: አብዮታውያን ደግሞ ደጋግመው እንደገለጹት

ከዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በፊት በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ሊመጣ የሚችለው የነዑስ ከበርቴው መደብና የአድሃሪው ቢሮክራሲ ህብረት የሚንፀባረቅበት የ"ወዝ አደር ፓር ቲ" እንጂ ሌላ ነገር ሊሆን አይችልም:: ለዚህ "ፓር ቲ" በግንባር ቀደምትነት የተሰለፉት አድርባይ ምሁራን ዓላማቸው ይህንን "ፓር ቲ" ካቋቋሙ በኋላ የተቀሩትን ህዝባዊና የሙያ ድርጅቶች በዚህ ቢሮክራሲያዊ ፓር ቲ ቁጥጥር ስር አውለው ከዚያ በኋላ <u>የመደራጀትን መብት የማይጨምር</u> የተገደበ ዲሞክራሲ "ለማወጅ" ነው::

የወዝ አደር ሊግ መሪዎች በዲሞክራሲ ጥያቄ ላይ የአብዮታውያንን መፈክር ተቃውመው ከዲሞክራሲ በፊት የ"ወዝአደር ፓር ቲ" እናቋቁም ይህን ካቋቋምን በኋላ በሙቁጥጥር ስር ዲሞክራሲ ለጭቁኖች በገደብ ይታወጅ ሲሉ በነበሩና በአብዮታውያን መካከል ያለው ልዩነት " አሁኑኑ ይታወጅ ወይንስ ነገ" የሚል የጊዜ ገደብን የሚመለከት ልዩነት አይደለም:: በሃቁ የወዝ አደር ፓር ቲ አመራር ስር በጠቅላላው በኢትዮጵያ የሚገኙ ፀረ ፊውዳል ፀረ ኢምፔሪያሊስና ፀረ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ሃይሎች በፓር ቲያቸውና በልዩ ልዩ ህዝባዊ ድርጅቶች ተደራጅተው ህዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ይመሰርቱ ? ወይንስ የሰፊውን ሕዝብ የመደራጀት መብት አፍነው የያዙ ጥቂት ነዑስ ከበርቴዎችና አድሃሪ ቢሮክራቶች " የወዝ አደር ፓር ቲ ነን" ብለው ዲሞክራሲ እስከታፈነ ድረስ ዞሮ ዞሮ በቢሮክራሲው ቁጥጥር ስር ከመውደቁ "ቢሮክራሲያዊ" ሕዝባዊ" ድርጅቶች ጥቂት መሪዎች ጋር "ህዝባዊ" አብዮታዊ ግንባር ብለው ፈጥረው የኢትዮጵያን ጭቁኖች መራራ ትግል ያጨናግፉ

በዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለአንዳች ገደብ አሁኑኑ የሚለው የአብዮታውያን መፈክር የመጀመሪያውን የትግልና የህዝባዊ ድል ጎዳና ያስይዘናል:: ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ተገድቦ የሚለው የወዝ አደር ሊግ መሪዎች አቋም በዲሞክራሲ መብቶችና በመደራጀት ጥያቄ መካከል ስላሉት ግንኙነቶች ካላቸው "አስደናቂ" አቋም ጋር ሲደመር ደግሞ እውነተኛውንና የኢትዮጵያን ጭቁኖች መራራ ትግል የሚያኮላሽ እስከዛሬ በመስዋዕትነት የተጎናጸፍናቸውን ድሎች እንዳልነበሩ አድርጎ የሚደመስስ የነዑስ ከበርቴውን መደብና የአድሃሪውን ቢሮክራሲ ድርጅታዊ "ውህደት" አጠቃ ፀረ ህዝቦችን በሃገራችን ላይ የሚያነግስ እንኳን ዲሞክራቶችንና አገር ወዳዶችን ወደ ትግሉ ሰብስቦ 95% የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚሰበስብ ቀርቶ ወዝአደሩንና አርሶ አደሩን እንኳን የአድሃሪው ቢሮክራሲ



ተቀጥያ የሚያደርገውን የክህደትና የፀረ አብዮት ጎዳና ያስይዘናል::

ታሪክ በመደብ ትግል በመጣ ጉዳይ ህብረት የሚሉ ነገር የለምና እንዲህ አይነት ክህደትና መንሸራተት እያለ ዛሬ "ተንሸራተቱ" የሚባሉት "ቀኝ መንገደኞች" የሚባሉት "ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ" በማለት ጓዶች የወደቁለትን የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም አንግበው በመታገል ላይ ያሉት አብዮታውያን ናቸው :: እንደሚታወቀው በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ አጨቃጫቂ ተብሎ የነበረው የዲሞክራሲ ጥያቄ በነ ዓለማየሁ ኃይሌ አሻጥር ዘገየ ከተባለ በኋላ ሰፊው ህዝብ በጥር ወር ወደ አጥቂነት እንደተሸጋገረ የዛሬ አድርባዮች በዲሞክራሲ ጥያቄ ላይ ከሁኑ ለየት ያለ አቋም ነበራቸው:: በዚያን ጊዜ በወጣው የማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች መረሃ ግብር ላይ አድርባዮችም አብረው ከሰፊው ሕዝብ ጋር ወደ አጥቂነት ተሸጋግረው እንደነበረ ይታወሳል:: እንኳን እንደዛሬው የክህደት አቋም ሊሰነዝሩ ቀርቶ አሁን ለማታዘብ ሰው እጅግ አስደናቂና ግንባር ቀደም አቋም ነበራቸው::

ትዝ ይለን እንደሆነ በየካቲት ወር 1969 ዓ.ም. ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ መሬት አንቀጥቅጥ የሆነ ቀይ ሽብርን በአድሃሪው ሰፈር እየነዛ ፀረ ሕዝብ ሃይሎች ጨርሶ መግቢያ ቀዳዳ ጠፍቶባቸው ውጭ ነፍስ ግቢ ነፍስ ላይ ነበሩ:: ይኸኔ አድርባዮችስ ምን ቀጣቸው ? ምንም የቀጣቸው ነገር የለም:: የታወቀውን የአድርባዮች መለያ ጠባይ በማንፀባረቅ የቀኝ አድርባዮች ከአየለው ሰፊ ሕዝብ ጋር አብረው አየሉ:: እንዲያውም "በግንባር ቀደምትነት" በመሰለፍ "የወደቀ ዛፍ ምሳር ይበዛበታል" እንዲሉ አድሃሪያኖች በይበልጥ እንዲጠቁ ወተወቱ:: ከዚህም አልፈው አድሃሪያች ገና በበቂ ያልተመቱ መሆናቸውን ለሰፊው ህዝብ በመጠቆም ህዝቡ የዚያን ጊዜ እጁ አስገብቶ ከነበራቸው ዲሞክራሲያዊ መብቶች በይበልጥ ማግኘት እንዳለበት በሰፊው አስታወቁ:: የኢትዮጵያ ማርክሲስት-ሌኒኒስት ድርጅቶች አብዮቱን ለመቀልበስ ያሰፈሰፉትን አድሃሪ ሃይሎች ለመምታት እንዲቻል ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለሰፊው ሕዝብ ባስቸኳይ እንዲታወጅ ለመታገል ባወጡት መረሃ ግብር ላይ ጠቅላላ በስምምነት ተገኙ::

ይህ ጠቅላላ ስምምነት ግን የሰፊው ሕዝብ ሰፈር እስኪጠቃ ድረስ ብቻ ነበር:: ቀስበቀስ አብዮታችን ወደ ተከላካይነት ሲያዘቅጥ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ መጠቃት ሲጀምር ዲሞክራሲ እየመነመነች ስትሄድ አድርባይ ምሁራን የታወቀው ጠባያቸው ከጠቃ ጋር ማጥቃት እንጂ ከሚጠቃ ሰፊው ሕዝብ ጋር ቆሞ ለአብዮቱ መዋደቅ ስላልሆነ የትላንትን ገንባር ቀደምትነት እንኳ ለነበረ ረስተው ከአድሃሪው ሰፈር መደባለቅ ለሲየለው ወገን ማደር ጀመሩ:: አድርባይ ማለት ወደ ነፈሰበት መገፈስ ወደ አየለው ተደባላቂ ማለት ነውና በደርግ ውስጥና ከደርግ ውጭ እያየለ ለመጣው ፀረ አብዮት አደሩ:: አብዮታችን ከአጥቂነት ወደ ተከላካይነት ሲዘፍቅ እየተመለከቱ አብዮታዊ ሚሊተንቶች በፀረ አብዮት ሃይሎች ጥይት እንደቅጠል ሲረግፉ እያዩ የአጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ቢሮክራሲ መሰል ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን እየያዙ ሲያገለግሉ እየታዘቡ የኢ.ዲ.ህ፣ የኢህአፓና ጠቅላላ አድሃሪዎች ቀጥር ነፍስ ገዳዮች በ"ሽምበል በሽምበል" እየተደረጉ ከእስር ቤት ሲለቀቁ እየተመለከቱ በክፍለ ሃገራትና በከተሞች የቀጥር ነፍስ ገዳይ ዝገብ እሽ ብለቻሃል እየተባሉ ታጋይ ወዝአደሮች የቀበሌ ተመራጮች የአብዮት ጥበቃ ጓዶችና ሌሎች አብዮታውያን በየእስር ቤቱ ሲወረወሩ እያዩ ... በነሱ ቤት አብዮት ለመቀልበስ "አስፍስፈዋል" ብለው የነበሩ ሃይሎች ዛሬ ጨርሰው ተደምስሰዋል:: ባስቸኳይ የተባለው ዲሞክራሲ ዛሬ በነሱ ቤት ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ተትረፍርፏል:: ስለዚህ "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ ለሁሉም" የሚለው መፈክር አሁንም በነሱ ቤት "የፈርጣጮችና" የቀኝ መንገደኞች" መፈክር እንጂ የአብዮት ጥያቄ አይደለም::

አድርባዮች ዛሬ ቀውለት የነበረውን የዲሞክራሲ ጥያቄ ለመሻር ከሁለት በሬ ወለደ አንዱን ለማሳመን አንድ ዓይነት ታአምር መፈለግ አለባቸው:: ወይም አብዮት ለመቀልበስ "አስፍስፈው" ነበሩ የተባሉ ሃይሎች ዛሬ መንም ነው ጠፍተዋል ወይ ደግሞ እነሱ ቢያይሉም ዛሬ ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ ሰፍኗል:: የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ሁሉቱንም በሬ ወለዶች በማያሳምን ሁኔታ የሚያስተባብል ነው:: ስለዚህ የቀኝ አድርባይ ምሁራን የሚቀራቸው ምርጫ ውይ ወደፊት ተራምደው ከአብዮታውያንና ከሰፊው ሕዝብ ጋር "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ ለሁሉም" ብለው መታገል ወይም ደግሞ "ዛሬ በቂ ዲሞክራሲ አለ ከዚህ በላይ አያስፈልግም" በሚለው መጋለጥና ወደ ታሪክ አተላነት መውረድ::



የአብዮታውያን ምርጫ ግልጽ ነው:: አብዮታውያን ዛሬ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ባለዲሞክራሲ እያገኙ ቃል በሰፊው ህዝብ ልጆች ደም ለተጻፈለት ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ታማኝ ሆነው ትግላቸውን ይቀጥላሉ የወደቁትን ታጋዮች አርማ አንስተው ተንሸራታቾችን ከሃዲዎችን ያለ ማወላወል እየተዋጉ ወደ ፊት ለፍትህ ለነፃነት ለጭቁን ህዝቦች አንድነት ወራራውን ትግል ፊትለፊት ይገጥማሉ:: ዲሞክራሲያዊ መብቶችን በሚመለከተው በኩል "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ ለሁሉም" የሚለው መፈክር ስር ተሰልፈው ይህንኑ ዓላማ በስራ ለመተርጎም በህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ከሁለት ዓመት ያህል በፊት ረቆ የተቀመጠው የዲሞክራሲ መብቶች አዋጅ ባስቸኳይ እንዲታወጅ ይታገላሉ:: የጭቁን ሕዝቦችን ዲሞክራሲያዊ መብቶች በመርገጥ በቢሮክራሲው አሻጥር የታፈኑ የህዝብ ተመሪዎችና ተራማጆች እንዲፈቱ ይታገላሉ:: አድሃሪው የሃይለስላሴ ቢሮክራሲ ህዝባዊ ድርጅቶችን ለማፈን በሚፍጨረጨርበት ቦታ ሁሉ ተደምስሶ በቦታው ሕዝባዊ ስልጣን እንዲተካ ይታገላሉ:: በመጨረሻም እንደገና የአብዮትን ሠፈር ጥራት ለማደፍረስ የሚፍጨረጨሩትን የቀኝ አድርባዮች ሙሉ በሙሉ ለማጋለጥ ተገቢ ወደሆነው ቦታቸው ወደ ታሪክ ትቢያ መጣያ እንዲገቡ ከሰፊው ሕዝብ ጎን ሆነው ትግላቸውን ያፋፍማሉ በዚህ ትግል የወሰደውን ጊዜ ይወስዳል እንጂ ሰፊው ሕዝብና አብዮታውያን ለጀመሩት ዓላማ እንደሚቀጥሉ በምንም አይነት መጠራጠር አይቻልም:: ተንሸራታቾች በሰፊው ሕዝብ ፊት ይጋለጣሉ ለዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ ለሁሉም እንታገላለን::

<u>በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ እሁኑኑ ምን ማለት ነው::</u>

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ትልቅ የትርምስ ነፋስ እየነፈሰ ነው:: በያዝነው ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ ቀውስ ከየአቅጣጫው ይታያል:: በፖለቲካም ሆነ በኢኮኖሚ እንዲሁም በሶሻል ጉዳዮች በሙሉ ይህ ነው የማይባል የተዘበራረቀ ሁኔታ እንዳለ የሚያከራክር አይደለም::

አብዮቱን ከውስጥ ሆነው የሚበረቡሩትን ሀይሎች ለሰፊው ሕዝብ ቁልጭ አድርጎ ለማሳየት የአካባቢውንና የዓለም አቀፍን የሃይል አሰላለፍ እንደዚሁ ቁልጭ አድርጎ ለማስገንዘብ፣ ይህንን በኢትዮጵያ አየር ላይ የሚያንዣብበውን ትርምስ ለአብዮቱ መገፋት ወደሚያመች ሁኔታ በፋጣኝ ለመቀየር መፍትሄው ዛሬ ፖለቲካዊ ብቻ ነው::

ዛሬ አገራችን የገባችበትን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የሶሻል ቀውስ ለትወጣው የምትችለው በመጀመሪያ ደረጃ ትክክለኛ የፖለቲካ መፍትሄ ባጭር ጊዜ ውስጥ የተገኘ እንደሆነ ብቻ ነው:: አብዮታችን የደረሰበትን ደረጃ ስንመለከትና አሁን ካለበትም ደረጃ በነቃ፣ በተደራጀና በታጠቀ ህዝብ ሃይል ላይ ተመርኩዞ ወደፊት እንዲገሠግሥ ከተፈለገ ብቸኛ የጊዜው አንገብጋቢ መፍትሄ ሆኖ የሚቀርበው የዲሞክራሲያዊ ሁኔታዎችን በፋጣኝ ማሟላት ነው:: ለዚህም ነው በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ እሁኑኑ የሚለው መፈክር የቅድምያ ቅድምያ ተሰጥቶት በፋጣኝ በሥራና በተግባር መተርጎም ያለበት::

በተለይ አብዮታችን በሚገኝበት የእድገት ደረጃ ላይ ይህንን መፈክር እንገብ እሁኑኑ በሥራ እንዲተረጎም መታገል የሚያስፈልገው፣-

1. <u>ቀለበሹን የፖለቲካ መስመር ለማጋለጥ ብሎም አብዮቱ ትክክለኛውን ፈር እንዲከተል ነው::</u>

በዛሬው የኢትዮጵያ ሁኔታ በደንፋው"ግራ"አድርባይ ኢህአፖ. ቀለበሽ የፖለቲካ መሥመር ላይ የማያባግም የፖለቲካ ዱላ ከተገኘ ወዲህ በሰፊው ሕዝብ ሰፈር ሠርጎ



የገባውንና በማንሰራራት ላይ ያለውን የቀኝ አድርባዮችንና የቢሮክራሲውን ቀለበሽ የፖለቲካ መስመር ሰፊው ሕዝብ እንዲነቃበትና እንዲቃወው ያስፈልጋል:: ለዚህም ተገቢር ዲሞክራሲያዊ መብቶች ተለቀው /ባሁኑ ጊዜ እነ.ኢ.ህ.አፖን ለማጋለጥ እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ የነበረው ዲሞክራሲ እንኳ ከመመገሙ የተነሳ አድሃሪያች በጣም አይለቀል/ ግልጽ የሆነ የሁለት መስመር ትግል መካሄድ አለበት:: በእንደዚህ ዓይነት ጠቃሚ የትግል ዘዴ በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግና በጠቃሚ ተራማጆች መካከል የለየላቸው አድሃሪያችና አድርባዮች ሊያሰፉት የሚሞክሩትን ቅራኔ አጥብቦ ፀረ ሰስት የሆኑትን ሃይሎች በሙሉ ሰብስቦ ያሰፈሰፈውን የአድሃሪያችን አጥቂነት በአንድነት ለመቋቋም ብሎም ለመደምሰስ ይቻላል::

በተለይ በምንገኝበት ወቅት የቀለበሽች የፖለቲካ መስመር ውዝግብር በያለበት በሚነዛበት ወቅት፣ በወዝአደሩ፣ በገበሬው፣ በወጣቱ፣ በሴቱ፣ በመለዮለባሹ፣ በቀበሌዎች ....ወዘተ የረቀቀ ከፋፋይና ፀረ አብዮት ሴራዎች በሚሸረቡበት ወቅት ይህን አደጋ አስመረዳት ወይም አርቆ የማስተዋል ችሎታን ለአብዮቱ ተቆርቋሪ የሆኑ ሃይሎች በሙሉ ካላሳዩ፣ ለአብዮቱ አዘቅት ውስጥ መግባት ታሪክ ፊት ተጠያቂ የሚሆኑበት ነው:: ስለሆነም ቀለበሽ የፖለቲካ መስመሮችን እያጋለጡ ለማሳጠርና አብዮቱን ለመቀጠል ዲሞክራሲ ብቸኛ መሣሪያ ሆኖ ቀርቧል::

2. <u>የሰፊውን ሕዝብ ንቃትና ድርጅት ለማዳበር፣ የመፍጠርና የውስብስብ ችግሮችን የመፍታት ችሎታውን ለማንቀሳቀስ::</u>

በኢ.ህ.አ.ፖ. ቀለበሽች ላይ ሰፊው ሕዝብ ፖለቲካዊ ዱላ ከተቀዳጀ በኋላ እነዚህን ዱላዎች አስጠብቆ ሕዝባዊ ድርጅቶችን አጠንክሮ የበለጠ ዱላዎችን ለመቀዳጀት መፈለጉን በይፋ አሳይቷል:: ይህም ህዝባዊ ገፊት መጥቆ ለመሄድ የሚያስችለውን ዲሞክራሲያዊ ጉዳና እንዲከፈትለት በተደጋጋሚ ጠይቋል:: እየጠየቀም ነው::

ይህንን የህዝብ ንቃተ ህሊና መዳበርና ድርጅታዊ ጥንካሬ እየጨመረ መምጣትን እንደጠር የሚፈሩት የለየላቸው አድሃሪያች የ" ተራማጅ"ካባ አጥልቀው ቀኝ አድርባዮችን ተገን አድርገው የአብዮቱን ገፊት ለመቅጨት ሲፍጨረጨሩ ይታያሉ::

እንግዲህ ሰፊው ሕዝብ በደርጉ ተራማጅ እርምጃዎች መወሰዱ በየአደባባዩ ደስታውንና አብዮታዊ ስሜቱን የገለፀውን ያህል በዛሬው ወቅት ለሚያነሳቸው

ጥያቄዎች ሰሚጀር ካጧና ከትግሉ መድረክ እንዲገለል ከተደረገ፣ አሁንም በአንዳንድ ቡታዎች መታየት እንደጀመረው አብዮታዊ ተሳተፈው እየመነመነ ከሄደ በዚህ ሁኔታ ከሰብ ሊደርሱ የሚችሉት ከበንት ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያን አብዮት ለመቀልበስ ያሰተኙት አድሃሪ ሃይሎች ብቻ ናቸው።

ስለሆነም ዛሬ ወዝ አደሩ መደብ በዲሞክራሲ እየታገዘ የአድሃሪያቹን ሰንሰለት እየበታተነ በደረሰበት ንቃተ ሕሊና የበለጠ ቅንጅት አለበት። ካሁን በበለጠ በቀያ ማህበረ ቁጥጥር እንዲኖረው ያስፈልጋል።እንዲሁም በምርት ላይ የበለጠ ቁጥጥር እንዲኖረው ያስፈልጋል። የወዝ አደሩ መደብ በዲሞክራሲ አሁኑኑ የመታገዝ መብት እስከሚያገኝ ድረስ እሩቅ ሳንሄድ የራሱ የሆነ ድርጅት እንኳ የሚቋቋም ማስጠበቂያ ከመሆን እየራቀ የቢሮክራሲው አሻጥ አውታር ሆኖ በራሱ ላይ ሲጉንበት ተመልካች ሆኖ ይቀራል።

የገበሬው ሕዝባዊ ድርጅቶች እንዲሁ የቢሮክራሲው ተቀጢላ እንዳይሆኑና ገበሬውን ከፍተኛ ንቃተ ሕሊና ለማድረስና የራሱን ችግሮች በራሱ ለመፍታት እንዲችል፣ እንዲሁም ባጠቃላይ ፀረ ሰስቶ የሆኑ መደቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች አብዮት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ መለቀቅ አለባቸው።

አሁን በምንገኝበት የትርምስ ሁኔታ ይህ መብት መለቀቅ የሕዝቡን የመፍጠርና ውስብስብ ችግሮችን የመፍታት ችሎታ ለማንቀሳቀስ ያስችላል። ሰፊው ሕዝብ በአብዮቱና በአገሪቱ ችግሮች ላይ በቀጥታ ተሳታፊ እስካልሆነ ድረስ አብዮት ፋይዳ አይኖረውም። ተአምር ሰሪ፣ ታሪክ አድራጊ ሰፊው ሕዝብ ነውና።

### 3. ቢሮክራሲውን ለመዋጋት

እንደሚታወቀው ሁሉ የመንግሥት ሥልጣንን መዋቅሮች በዙ ዝርዝር ውስጥ ሳይገባ ከሞላ ጎደል በሁለት ዋና ክፍሎች ለይቶ ለማስቀመጥ ይቻላል። የመጀመሪያውና ዋነኛው የፖለቲካ ሠሪውና ወሳኝነትን የሚያጠቃልለው ክፍል ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የተወሰነውን ፖለቲካ አስፈጻሚው ክፍል ነው።



እንግዲህ እነዚህ አካሎች የመንግሥት ሥልጣን የጨበጠው መደብ በሌሎች መደቦች ላይ የበላይ ገዢነትን የሚያረጋግጥባቸው፣ ባንድ በኩል ለመደቡ የሚጠቅመውን ፖለቲካ የሚወስንባቸውና በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን ውሳኔ በተግባር የሚያስተረጉምባቸው አውታሮች ናቸው።

እነዚህም የመንግሥት መኪና ሁለት ክፍሎች ለአንዱ መደብ እስከዛሬ ድረስ እጅግ በጣም የተያያዙና ተቀነባብረው የሚሠሩ የአንድ መንግሥት መኪና መዋቅሮች ናቸው ። የሁለተኛው ለአንደኛው ታዛዥ ሆኖ የሚሠራበትና አንደኛው ደግሞ የሚወስነው ፖለቲካ ለሁለተኛው ተስማሚ ሆኖ የሚቀርብበት ሁኔታ በግልጽ ያንፀባርቃል ማለት ነው። ለምሳሌ ከበርቴው መደብ የመንግሥት ሥልጣን በጨበጠባቸው አገሮች ውስጥ በአገሪ ፕሬዚዳንትና በሚኒስትሮች የበላይነት የሚወሰነው ኢኮኖሚያዊ፣ ወታደራዊ ...ወዘተ ፖሊሲ ለከበርቴው ሸንጎ ቀርቦ ከፀደቀ ወዲህ በተግባር ለመመንዘር ወደ ልዩ ልዩ መንግሥታዊ ተቋሞች /ፋይናንስ፣ ሚሊተሪ፣ ፖሊስ...ወዘተ/ ተላልፈው ለወዛደሩ መደብ መጨቆኛ ይውላሉ።

ይሁንና እንደ ኢትዮጵያ በመሸጋገሪያ ወቅት ላይ በሚገኙ አገሮች ማለትም በአንዱ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሳቢያ አንዱ መደብ ከመንግሥት ሥልጣን ደረጃ ተገርሥሶ ሌላ መደብ ሲተካው፣ ከፍ ብለን ያየናቸው የመንግሥት መኪና ሁለት ክፍሎች የመሸጋገሪያው ወቅት እስካላከተመ ድረስ ተግባብተው ተቀነባብረው ሊሠሩ አይችሉም። ለምሳሌ የፖለቲካ ሥልጣኑን የጨበጠው ንዑስ ከበርቴ ደርግ ሃይለስላሴ ከወደቀበት ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው የመሸጋገሪያ አብዮታዊ መአበል ውስጥ በሰፊው ሕዝብና በጠቀኛ ተራማጆች ግፊት ደርግ ውስጥ ጥቂት ባሉ ተራማጆች አማካይነት የወሰዳቸውን አብዮታዊ እርምጃዎች/ የመሬት አዋጅ ... ወዘተ/ ፣ የተገማማው የኢምፔሪያሊዝምና የፊውዳሊዝም ፍጡር የሆነው ቢሮክራሲ በሥራ እንዳይተረጎሙ ያደረገውንና አሁንም የሚያደርገውን አሻጥር መመልከቱ ይበቃል። ባንድ ቃል እስከ ተወሰነ ደረጃ ድረስ ደርግና ቢሮክራሲው ቅራኔ ገብተው ነበር ማለት ነው።

እንግዲህ ከየካቲት 66 ጀምሮ ኢትዮጵያ ውስጥ በግልጽ እንደታየው ሁሉ ከፖለቲካ ወሳኙ አካል/ደርግ/ የወጡት ውሳኔዎች አብዮታዊ እስከሆኑ ድረስ የሥራ አስፈፃሚው አካል / አድሃሪው የሲቪልና የሚሊተሪ ቢሮክራሲ/ ለፖለቲካ ወሳኙ አካል ፈጽሞ እንደማይታዘዝለትና በሎም እንደሚዋጋው ነው። ከየአቅጣጫው የተደረጉትን የፖለቲካና የኢኮኖሚ አሻጥሮች፣ የመፈንቀለ መንግሥት ሙከራዎች... ወዘተ መመልከት ይበቃል።

ይህ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የሚያሳየን አንዱ የታሪክ ጠቀ ምንጭነው ቢባል ሳንቆም ያልተነካው አሮጌው የተገማማ ቢሮክራሲና በመንግሥት ስልጣን ደረጃ የፖለቲካ መወሰናውን አካል የጨበጠው መደብ መካከል ቅራኔዎች እንዳሉና እነዚህም ቅራኔዎች ደርጉ ወደ ሰፊው ሕዝብ ከተጠጋ እንደሚሰፉና ደግሞ ወደቢሮክራሲው ሲቀርብ ደርግና ሰፊው ሕዝብ መካከል ያሉት ቅራኔዎች እየሰፉ እንደሚሄዱ ነው:: ምክንያቱም ሰፊው ሕዝብ ካለምንም መወላወል ፀረ ቢሮክራሲ ነውና :: ደርግና ቢሮክራሲው መካከል ያለው ቅራኔ እየሰፋ በነበረበት ወቅት አብዮታዊ እርምጃዎችን ለማስፈጸምና አብዮቱን ለማራማድ አዳጋች ፀረ ቢሮክራሲ የሆኑ ህዝባዊ ተቋሞች አስፈላጊ ሆነው ተገኝተው እንደነበረ ይታወሳል:: ፀረ ቢሮክራሲና አብዮታዊ የነበረው የቀድሞ ሕዝብ ድርጅት ጽ/ቤት፣ አሁን እነ ኢህአፖና ቀኝ አድርባዮች ቁጥጥር ስር እየዋሉ የመጡት ግን በወቅቱ ህዝባዊነታቸውን በግልጽ ፀረ ቢሮክ አቋም ላይ ያረጋገጡት ቀበሌዎች ... ወዘተን ለመጥቀስ ይቻላል::

ዛሬ ግን የኢትዮጵያ አየር ላይ የሚነፍሰው የቀለበሳ ነፋስ በበጎት ትግሉና መስዋእትነት የተገኙትን ድሎች ለማዳፈን አብዮቱን ለመቀልበስ ፣ የተገኙትን ሕዝባዊ መዋቅሮች ለመገደልና ለቢሮክራሲው እጥዷ የተመነሱ ለመሆናቸው ለማገም ጠቋሚ አስተያየ ግልጽ ነው:: ደርግም ይህንን ጠቀ ተረድቶ አብዮታዊ ነኝ እስካለ ድረስ ከሰፊው ሕዝብ ወገኖች ጋር አድርጉ ቢሮክራሲው ላይ መዝመት ይኖርበታል:: ዛሬ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ እሁኑኑ ይለቀቁ ሲባል፣ ቢሮክራሲው ይውደም ይደምሰስ ሲባል አድሃሪው ቢሮክራሲ በፍጹም በሥራ ሊተረጉማቸው የማይችላቸውን የፖለቲካ ውሳኔዎች /አብዮታዊ እስከሆኑ ድረስ/ ሰፊው ህዝብ ይተርጉማቸው ማለት ነው:: ዲሞክራሲ እስከታፈነ ድረስ ቢሮክራሲው ይነግሥ ማለት ነው:: እንግዲህ ጊ/ወ/አ/ደርግ አሁንም ከሰፊው ሕዝብ ጎን ቆም ያለሁ የሚል ከሆነ ቢሮክራሲውን ለመታገል ዲሞክራሲያዊ መብቶችን አሁኑኑ መለቀቅ ይኖርበታል:: ዲሞክራሲያዊ መብቶችም ተለቀው በሚገባ በሰፊው ሕዝብ አውታሮች አማካይነት በሥራ እንዲተረጐሙ አስፈላጊውን እንክብካቤ ማድረግ ይኖርበታል:: ስለፋን ከተገማማው ቢሮክራሲ ጋር ማድረጉን እየመረጠ በዚሁ ከቀጠለ ሰፊውን ሕዝብ መፍራቱንና አብዮት የሚባል ነገር ከንግዲህ ለመስማት አለመፈለጉን በይፋ ያስታውቃል ማለት ነው:: ምክንያቱም ከፀረ አብዮት ሃይል ጋር እርቀ ማድረግን መርጧል ማለት ነውና::

በተለይ የሲቪሉና የሚሊቴሪው ቢሮክራሲ ከቀን ወደቀን እየደለበ ሲሄድ ስለሚታይ የአብዮቱና የአገሪቱ ህልውና አደጋ ላይ መውደቁ ዛሬ ለማንም እየተከሰተ የመጣ ሃቅ ነው:: ይህ ቀላል ያልሆነ የቀለበሳ አደጋ ለጊ/ወ/አ/ደርግ ለራሱ ይዋል ይደር እንጂ ቀጥተኛ አደጋ መሆኑ አይቀርም:: ከዚህ አስጊ ሁኔታ ለመውጣት አሁንም ዲሞክራሲ ብቸኛ መንገድ ነው::



## 4. ለሐቀኛ ተራማጆች ሕብረት

ዛሬ ወደድንም ጠላንም ቀኙ በኢትዮጵያ እጅግ በጣም ተጠናክሯል:: ከበረቱ የጠነከረ ሐቀኛ የተራማጆች ህብረት ከምንጊዜም የበለጠ አስፈላጊና አጣዳፊ የሆነበት ወቅት ነው:: ለሐቀኛ ተራማጆች ህብረት፣ ውህደትና መጠሪያ በመገ ከድርጊት ጋር በጽኑ አቋህደ የያዘ ሐቀኛ የወዝ አደር ፓርቲ እንዲመሠረት እውነተኛ ተራማጆች ይታገላሉ:: ለዚህም ለተቀደሰ ዓላማ የተሰለፉ ሃይሎች በሙሉ ከዛሬ ጀምሮ ሂደቱን በጠራ መልክ ለመቀጠል መቻል አለባቸው:: ተራማጆች መካከል ያለውን ቅራኔ ማባባስና ማስፋፋት ዛሬ የሚጠቀመው ፀረ አብዮትን ብቻ ነው:: ስለዚህም ተራማጆች በሙሉ ቀዳሚ የአብዮቱ ጠላቶች ላይ መነጣጠን ቀጥለው እነሱ መካከል ያለውን ቅራኔ ለመፍታት ዛሬ ግልጽ የሆነ ዲሞክራሲያዊ ውይይት ማድረግ አለባቸው::

## 5. የብሔረሰቦችን ጥያቄ ለመፍታት

ዛሬ ከፍተኛ ውዝግብር ከመኖሩ የተነሳ እንደሚታየው ሁሉ ተምክህተኞችም፣ ጠባብ ብሔረተኞችም የሚምሉትና የሚገዘቱት በማርክሲስዝም ሌኒኒዝም ነው:: የብሔረሰቦችን ጥያቄ ከብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት አገባር ለመፍታት እንዲቻልና ሰፊውም ሕዝብ ትክክለኛውን መፍትሄ አምኖ እንዲጨብጠው ለማድረግ ዲሞክራሲያዊ መብቶች እጅግ በጣም አስፈላጊ ሆነው ቀርበዋል:: ዛሬ ዲሞክራሲ ባለመለቀቁ ብቻ የተነሳና የብሔረሰቦችን እድል በአድሃሪው ቢሮክራሲ አማካይነት ለመፍታት በመታቀዱ ሰፊው ሕዝብ ከአብዮቱ እየራቀ ሲሄድ ይታያል::

## 6. የኢኮኖሚና የበሸል ችግሮችን ለመፍታት

ኢትዮጵያ የገባችበትን ትልቅ የኢኮኖሚ ቀውስ ዛሬ ማንም የሚያውቀው ነው:: ይህንንም ቀውስ በቀጡ ለመወጣት እስከዛሬ ድረስ አመቺ ሁኔታ ባለመፈጠሩ ቀውሱ እየተባባሰ ሲሄድና አገሪቷ አዘቅት ውስጥ እየገባች ስትሄድ ይታያል:: አስፈላጊ የሆኑ ሸቀጦች ዋጋ ሸቀብ እየጨመረ መምጣትና እንዳንዱም ከገበያ መጥፋታቸው፣ በገጠርም ሆነ ከከተሞች በየጊዜው የሚታይ ሁኔታ ሆኗል:: ገበሬው በከተሞች የሚያስፈልጉትን ሸቀጦች እንደልቡ ስለማያገኝና ቢያገኝም በጣም ስለሚ ወደድበት መንግሥት ባወጣው አነስተኛ የተመን ዋጋ እህሉን መሸጥ አወክታል::

ለዚህም ችግር ዋና ተጠያቂዎች አሻጥረኛ ነጋዴዎችና ቢሮክራቶች መሆናቸው እየታወቀ ግልጽ ዲሞክራሲያዊ ውይይት ለማድረግ ባለመቻሉና አድሃሪያችን ለማጋለጥ ስላልተቻለ ይህ ችግር እየተባባሰ መሄዱ የማይቀር ነገር ነው።

በጦርነቱ ሳቢያ የተፈጠሩትንም ችግሮች በደንብ ለመወጣት አመቺ ሁኔታዎች አስቀድመው መፈጠር አለባቸው። ለዚህ ሁኔታ መፈጠር ዲሞክራሲ የቅድሚያ ቅድሚያ ቦታ የሚይዝ የፖለቲካ መፍትሄ ነው።

7. <u>ዛሬ ዲሞክራሲ ማለት</u>

በዚህ በተዘረዘረ ሁኔታ በመጠቀም ቁልፍ ቦታዎችን ሊይዙ የቻሉትን ቢሮክራሲውንና የኢህአፓ ሠርጎገቦች ከቀበሌዎችና ሕዝባዊ ድርጅቶች ...ወዘተ እንደነበረ ለማውጣት እንዲቻልና በእሥር ላይ የሚገኙትን የቁኝ ተራማጆችን ወዝ አደሮችን፣ ገበሬዎችን፣ ወጣቶችን፣ሴቶችን፣ መለዮ ለባሾችን ባስቸኳይ መፍታት ማለት ነው።

ዛሬ ይህ የተዘረዘረ ሁኔታ ለአብዮቱ አመቺ ወደሆነ ሁኔታ ለመቀየር ካልተቻለ፣ አብዮቱ በፊር ውስጥ ሠርገው የገቡትንና ወቸገበር የሚነዙትን አድሃሪ ሃይሎች በሙሉ ለመደምሰስ ካልተቻለ፣ አብዮቱ ይቀለበሳል።

ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ
አብዮትን ከቀልበሳ ለማዳን !

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ
The Ethiopian Students' Union in Europe
Editorial Board

## ማሳሰቢያ

ውድ አንባቢያችን፣

የጠውን ንቅናቄ ከውስጥ ሆኖ ቦርቦሮ ለማደከም ያደረገው ሙከራ ስላልተካካለት እርሱን ከንቅናቄያችን ያገለለው ፀረ ሕዝብ ቡድን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፣ከአስር ዓመት በላይ ሰፊው ሕዝብ ጎን በመሰለፍ ያለማቋረጥ ያለመታከት ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ፊውዳሊስት ትግሉ ሲያካሄድ በኖረው ማህበራችንና በነዚህም አስር ዓመታት ያለተቋረጠውን ነፃነት በመንጠቅ የሰፊውን ሕዝብ ድምፅና ትግል ሲያስተጋቡ በኖሩት ፣ከየትናንሽ የተማሪ ማህበራት መጽሔት በላይ የሰፊው ሕዝብ ማስተማሪያና መቀስቀሻ ሆነው በቆዩት በታጠቅና በትግላችን ስም መጠቀም ጀምረዋል።። የዚህ ፀረ ሕዝብ ቡድን ዓላማ ማህበራችን እንዲሁም ታጠቅና ትግላችን በአስር ዓመት ቆራጥ ትግል ባተረፉት ስም ተጠቅሞ ፀረ ሕዝብ ፖለቲካውን ለመሸፈን ነው።።እንዲሁም ከውስጥ ሆኖ ያታለውን የኢትዮጵያ ተማሪያችና ተራማጆች አንድነት የማፍረስ ሙከራ ከውጭ ሆኖ ወሬነገር በመንዛት ለማፋፋም ነው።።ይህም እንደማይሳካ የተረጋገጠ ነው።። ለማገናዘብ፣የተለመደው መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ አድራሻ/ማለትም P.O.BOX 3198 10364 STOCKHOLM - SWEDEN ያለ ያዙ፣የዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪያች ማህበር አባልነትን የማያመለክቱ ገን የማህበራችን መጽሄቶች ስም የያዙ መጽሄቶች ወዘተ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪያች ማህበር መጽሄቶች አለመሆናቸውን እንድታውቁልንና እንድታስታውቁልን እንጠይቃለን።።ለእነዚህ አይነት መጽሄቶች ተመያዥ ··ዓለም ዓቀፍ ፌዴሬሽን·· በሚባለ ስም የታወቀው የነ አሰፋወሰን — መንገሻ ሥም የወጣቶች ድርጅት ነው።።

ከፋፋዮችና አወናባጆች ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ይውደሙ!
የእውነተኛ አብዮታዊያንና ተራማጆች አንድነት ይኑር!
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው!

በአሊተማ መጽሄት አዘጋጅ ቦርድ